የሥነ-ሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና የተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


ድኅረ ምረቃ መረሃ ግብር

# የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት

<u>በ</u>


አበበ ሾይሻ


ነሐሴ/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሥነ-ሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና የተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


ድኅረ ምረቃ መረሃ ግብር


በ

አበበ ሾይሻ


በአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


አማካሪ

ጌታሁን አማረ (ፕ/ር)


ነሐሴ/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሥነ-ሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና የተግባቦት ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## ድኅረ ምረቃ መረሃ ግብር

የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ለኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት በሚል ርዕስ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአበበ ሾይሻ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

<u>በ</u>

**አበበ ሾይሻ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

**አማካሪ :- <u>ጌታሁን አማረ (ፒ/ር)</u> ቀን------------------------------ ፊርማ------------------------**

**ፈታኝ፡- <u>ሙሉሰው አስራተ (ዶ/ር)</u> ቀን----------------------------------ፊርማ--------------------**

**ፈታኝ፡- <u>ስለሺ አባተ (ዶ/ር)</u> ቀን--------------------------------------ፊርማ---------------**

**ነሐሴ 2016 ዓ.ም**

አዲስ አበባ

# ማረጋገጫ

የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ለኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ ሳይንስና ሥነ-ሰብ ኮሌጅ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የተደረጉና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡

ስም-----------------------------------------

ፊርማ--------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን------------------------

## ምስጋና

ከሁሉ በፊት ይህንን ጥናት ጀምሬ እንዳጠናቅቅ እና ለመቋቋም በሚከብድ ሀዘንና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ አልፌ ለዚህ እንድደርስ ጉልበት ለሆነኝ ልዑል እግዚአብሔር እስከ ዘለዓለሙ ምስጋናና ክብር ይሁን። አሜን!!

በመቀጠል የዚህ ጥናት ርዕስ የመጨረሻ ቅርጽ ከማስያዝ ጀምሮ ግድፈቶችን በማረም፣ ስህተቶችን በመጠቆም ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ እስከ ጥናቱ ማጠናቀቂያ ድረስ ገንቢ አስተያየት በመስጠት፣ አባታዊ ምክር በመለገስና ሂደቶችን በማሳየት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለመምህሬና አማካሪዬ ለፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬ ከልብ ነው።

ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ወጪ በመሸፈን ትብብር ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውለታው የሚረሳ አይደለም። ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት፣ መጽሐፍ ላዋሳችሁ መምህራን፣ ተስፋ በቆረጥኩ ጊዜ ከአጠገቤ ሳትለይ ያበረታታሽኝ ውድ እናቴ ባልፀነ ባቦ፣ ለራሱን ጉልበትና ገንዘብ ሳይሳሳ ሁለም ከጎኔ ላልተለየኝ ውድ ወንድሜ አማኑኤል ሾይሻና ሌሎች ቤተሰብ አባላት እንዲሁም ጓደኞቼ ልባዊ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ።

# አጠቃሎ

በዚህ ጥናት ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ተገምግሟል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የቋንቋ ምሁራን ያቀረቧቸውን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ተገምግሟል፡፡ ጥናቱን ከዳር ለማድረስ ሰነድ ፍተሻ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የተገኙ መረጃዎች አይነታዊ ምርምር ዘዴን በመጠቀም በገላጭ ስልት ተተንትነዋል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የይዘቶቹ አቀራረብ በተመለከተ በታላሚዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከቅደም ተከተላዊ አካሀድ አንጻር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ከቀረበው ይልቅ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ዘዴ የቀረበው ይዘት አብዛኛውን ክፍል የሚሸፍን ሲሆን ከትኩረት አንጻር ደግሞ ውጤት ተኮር በሆነ መንገድ ከቀረበው ይልቅ በሂደት ተኮር ዘዴ የቀረበው ሰፍውን ክፍል እንደሚሸፍን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከአደረጃጀት አንጻር ደግሞ አብዛኛዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች እየተደጋገሙ መቅረባቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ምንም እንኳን ይዘቶቹ ሚዛናዊና ተመጣጣኝ ባይሆኑም ሁሉንም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መንገዶችን አካተው መያዙ፤ ሰዋስው ይዘቶቹ በምሳሌዎች እየታገዙ መቅባቸው፣ ወዘተ እንደ ጠንካራ ጎን የታዩ ይዘቶች ሲሆን የቃላት ትምህርት ከአውድ ውጪ መሰጠት፣ አንዳንድ መመሪያዎችና ይዘቶች ግልጽ አለመሆን፣ የተወሰኑ ይዘቶች መቅረብ የሚገባው መርህ እያለ ያለብስለት መቅረብ፣ ወዘተ እንደ ደካማ ጎን የተነሱ ናቸው፡፡ በተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ ተከታታይነት ኖሯቸው የተደራጁ ቢሆኑም ድግግሞሽ አግኝተው የተደራጁ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሁሉም ምዕራፎች እና ክፍል ደረጃዎች ተከታትለው አለመደራጀታቸውን፤ "በአረፍተ ነገር" ላይ የሚያተኩሩ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም የአቀራረብ ለውጥ (ተለጣጣቂነት) ይዘው ተደራጅተዋል፡፡ ባጠቃላይ በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው ተደራጅተው የቀረቡ ሲሆን በሁሉም አቀራረብና አደረጃጀት ስልቶች መቅረባቸው የሚበረታታ ነው፡፡ በመጨረሻም በይዘቶቹ አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ የታዩ ደካማ ጎኖችን ለማሻሻል ይረዳሉ ተብለው የታመኑባቸው መፍትሄ ሀሳቦች ተሰንዝረው ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ I
አጠቃሎ ........ II
ማውጫ ........ III
ምዕራፍ አንድ
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 4
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 5
ምዕራፍ ሁለት
ክለሳ ድርሳናት ........ 7
2.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ........ 7
2.2 ሰዋስውና የሰዋስው ትምህርት ........ 10
2.3 የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ........ 12
2.3.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ........ 12
2.3.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ........ 13
2.3.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ ........ 13
2.3.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ ........ 14
2.4. የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ........ 14
2.4.1 ተከታታይነት (Continuity) ........ 15
2.4.2 ተለጣጣቂነት (Sequence) ........ 15
2.5 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 16
ምዕራፍ ሶስት
የአጠናን ዘዴ ........ 22
3.1 የመረጃ ምንጭ ........ 22
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ........ 22
3.3 ናሙና አወሳሰድ ........ 22

3.3.1 የመማሪያ መጻሕፍት ናሙና አውሳሰድ ........................................................ 22
3.3.2 የክልልና የክፍል ደረጃ ናሙና አመራጥ ........................................................ 23
3.4 መረጃ መተንተኛ ዘዴ ........................................................ 24

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና ........................................................ 25

4.1 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ........................................................ 25
4.1.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ........................................................ 25
4.1.1.1 በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........................................................ 25
4.1.1.2 በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........................................................ 29
4.1.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ........................................................ 32
4.1.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ ........................................................ 34
4.1.3.1 በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........................................................ 34
4.1.3.2 በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ........................................................ 36
4.1.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ ........................................................ 39
4.1.4.1 በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ........................................................ 39
4.1.4.2 በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ........................................................ 44
4.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ........................................................ 45
4.2.1 ተከታታይነት ........................................................ 45
4.3.2 ተለጣጣቂነት ........................................................ 48
4.3 መማሪያ መጻሕፍቱ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ተዛምዶ ........................................................ 51

ምዕራፍ አምስት ........................................................ 53

ማጠቃለያና አስተያየት ........................................................ 53

5.1 ማጠቃለያ ........................................................ 53

5.2 አስተያየት ........................................................ 55

ዋቢ ጽሐፎች ........................................................ 56

## ሠንጠረዥ ማውጫ


<u>ርዕስ</u> <u>ገጽ</u>

ሰንጠረዥ 1. በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሰዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ ገለጻ የተሰጠባቸው ርዕሰ ጉዳዮች የሚያመለክት፦....................................................26

ሰንጠረዥ 2. በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሰዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ ገለጻ የተሰጠባቸው ርዕሰ ጉዳዮች የሚያመለክት፦............................................29

ሰንጠረዥ 3. በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ ሁኔታ ............................................................................45

ሰንጠረዥ 4. በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ ሁኔታ ............................................................................46

ሰንጠረዥ 5. ተተኪ መማሪያ መጽሐፍት ከደቡብ ክልል ትምህርት ብሮ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና----------------------------------51

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ውስጥ ከመሰሉ ጋር ምኞት ተስፋውን፣ ሀዘን ደስታውን፣ እውቀት ሙላቱን፣ ፍቅር ጥላቻውን፣ ወዘተ የሚያጋራበት መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ ከማህበራዊ መስተጋብር በተጨማሪ በትምህርት ዓለም ሲታሰብ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ባንድ በኩል ተማሪው የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት በቋንቋው አማካኝነት ለማግኘት ይረዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋው እንደ አንድ ትምህርት አይነት በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች ስለቋንቋው እውቀት እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል። ስለቋንቋው እውቀት ይኖራቸዋል ሲባል "የቋንቋውን ውስጣዊ አወቃቀር፣ የአሰካክ፣ የዓረፍተ ነገሮች አቀነጃጀት ስርዓት፣ ወዘተ ለይቶ ማወቅን የሚመለከት ነው"(ጌታሁን 1990:V)።

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ቋንቋ የሀሳብ ማስተላለፊያ ወይም መቀበያ መንገድ ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚው ስለቋንቋው ሁለንተናዊ እውቀት ኖሮት የሚገለገልበት መሆኑን ያመላክታል። በመሆኑም ቋንቋዉ እንደ አንድ ትምህርት መሰጠቱ ተማሪው ስለቋንቋው በቂ እውቀት ኖሮት ከማህበራዊ አጠቃቀሙ ጋር አዋህዶ እንዲጠቀም ያስችለዋል።

እንደ ባየ (2002፡13) የቋንቋ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋው ጥሩ አድማጭ፣ የተሻለ ተናጋሪ፣ ጥሩ ጸሐፊና አንባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ የሥነ-ልሳን እና የሥነ-ጽሁፍ እውቀት ለማጎልበት ነው። ይህ ማለት የትምህርቱ ዓላማ ቋንቋው በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ያለው አገልግሎት ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የቋንቋውን ውስጣዊ አወቃቀር ሥርዓትና አጠቃቀም ለይቶ ለማሳወቅ ያለመ መሆኑንም ጭምር መረዳት ይቻላል። ከአወቃቀር ሥርዓቶች መካከል አንዱ ደግሞ ሰዋስው ነው። ሰዋስው የማንኛውም ቋንቋ መሠረት ከሆነው ድምፅ እስከ ዓረፍተ ነገር አወቃቀር ድረስ ያለውን ሰፊ መዋቅር የሚይዝ መሆኑን (ባየ 2002፡13) ገልጸውታል።

ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ሰዋስው ሲባል የአንድ ቋንቋ መሰረት ከሆነው ከድምጽ አንስቶ ቋንቋው በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ያለውን አገልግሎት ድረስ ያለውን ሰፊ መዋቅር የሚመለከት መሆኑን ያመላክታል። ድምጽ በሥርዓት ተቀናጅቶ ቃላትን፤ ቃላት በሥርዓት ተቀናጅቶ ሀረግን፤ ሀረጋት በሥርዓት ተቀናጅቶ አረፍተ ነገርንና እነዚህ አረፍተ ነገሮች ደግሞ

በቋንቋው ተጠቃሚ ማህበረሰብ ዘንድ የሚኖረውን ትክክለኛውን አጠቃቀም ሂደትን የሚመለከት መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ሲባል የቋንቋው ተጠቃሚ ማንኛውም ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ በቋንቋው እየተገለገለ እያለ ከቋንቋው ትክክለኛ አጠቃቀም ሂደት ወይም አነጋገር ሥርዓት ቢወጣ (ቢሳሳት) ስህተቱንና እንደት መስተካከል እንዳለበት አጠቃላይ ሥርዓቱን የሚመለከት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይህንን የቋንቋ አጠቃላይ ሥርዓት በዋናነት ለይተው አውቀው መገልገል የሚችሉት የዚያ ቋንቋ አፍ ፈቶች ቢሆኑም ኢ-አፍ ፈት የሆኑት ደግሞ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ጋር በሚኖረው ተከታታይ በሆነ ማህበራዊ መስተጋብርና ወደ ትምህርት ቤት በመግባት የሰዋስው እውቀት መካን ይችላሉ፡፡ በመሆሁም የሰዋስው እውቀት በሰው ልጆች አዕምሮ ውስጥ ያለና መኖሩ የማይታወቅ ወይም በትምህርት የተገኘ አውቀት ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም በትምህርት ዓለም ውስጥ አንድን ቋንቋ በአፍ መፍቻነትም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማር ተማሪ የታላሚውን ቋንቋ ሥነ-ልሳናዊ እውቀት ሊያዳብርበት የሚችለው የሰዋስው ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ሁለቱ የተማሪ ቡድኖች (አፍ ፈትና ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ) የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው በሚማሩበት ዓላማ፣ ወደትምህርቱ ይዘውት በሚመጡት የሰዋስውና የእውናዊ ዓለም እውቀት አይነትና መጠን፣ ወዘተ ጉዳዮች የተለያየ በመሆኑ የተለያየ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ስልት እንደሚያስፈልጋቸው (Batston 1994፣ እና Ur 1996) ያደረጓቸው ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

ስለሆነም የአንድ ቋንቋ ባለቤት መሆን ይቻል ዘንድ የዚያ ቋንቋ የሰዋስው እውቀት አስፈላጊ መሆኑ የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የአንድን ቋንቋ ቃላት እንዴት ባለመልኩ መቀናጀት እንዳለባቸው ካላወቅን በቃላቱ ላንጠቀም ወይም ላንግባባ እንችላለን (Ur 1996፡ 46)፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በአንድ ቋንቋ ሥርዓት ላይ ችሎታ ወይም እውቀት ከሌለን ወይም የቋንቋውን ሰዋስው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ካላወቅን በቋንቋው የሚናደርገው የትኛውም አይነት ሙከራ ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም የአንድ ቋንቋ ሥርዓታዊ የመግባቢያ መሳሪያ እንዲሆኑ ካስቻሉት መንዶች ዋነኛው ሰዋስው በመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ (ጌታሁን 1990፣v) "ክህሎትንና ሥርዓትን አቀናጅቶ ያስተማረ መምህር ቋንቋውን በተሟላ ሁኔታ አስተምሯል፣ ተማሪውም የተሟላ እውቀት አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡" ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የቋንቋውን ክህሎችና ሰዋስውን የሚነጠሉ ሳይሆኑ

አንዱ ሌላውን የሚደግፍና ሁለቱን አቀናጅቶ ማስተማር የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ወሳኝ መሆን ያመላክታል፡፡

ይህን የትምህርት ዓላማ ለማሳካት የትምህርት ይዘቶቹ በተደራጀ መልክ ከሚሰጥባቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የተማሪ መማሪያ መጻሕፍት ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የመማሪያ መጻሕፍት በትምህርት አይነት የሚዘጋጁ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ተጣቃሽ ናቸው፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በጥንቃቄ የተመረጡና የተደራጁ ይዘቶችን ለተማሪዎች ማቀረብ ይችል ዘንድ በዝግጅት ወቅት ይሁን ስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ወይም ፍተሻ ሊደረግባቸውና ከዚህ በሚገኙ ምላሾች ሊሻሻሉ እንደሚገባ cunningsworth (1995) ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው ለየትኛውም ክፍል ደረጃ በሚዘጋጁ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚካተቱ ትምህርት ይዘቶች ላይ ተደጋጋሚ ግምገማ በማካሄድ የትምህርቱን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ማዘጋጀት ጠቃሚ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሀገራችን አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተቀርጾ በተግባር ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ክልሎች ካላቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ለመካከለኛ ደረጃ (7ኛ እና 8ኛ ክፍል) የተማሪ መማሪያ መጻሕፍት ያዘጋጃሉ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከእነዚህ መካከል አንዱ ነው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትም ቋንቋው በተለያዩ ክልሎች ያለውን የአገልግሎት ደረጃና የተማሪዎች ችሎታ መሰረት በማድረግ ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህም አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ እና አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚል የተዘጋጁ ሲሆን አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ በሚል የተዘጋጀው አፋቸውን በዚያ ቋንቋ ለፈቱት የተዘጋጀ ነው፡፡ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋው በሚል የተዘጋጀው ደግሞ አፋቸውን በሌላ ቋንቋ ለፈቱትና ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩት የተዘጋጀ ነው፡፡

በመማሪያ መጻሕፍቱ በአራቱ የቋንቋ ክህሎች ላይ፣ በሥነ-ጽሁፍ፣በሥነ-ልሳን እና በቃላት ላይ የሚያተኩሩ ይዘቶች ተካተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ይህ ጥናት የስነ-ልሳን እውቀት ዘርፍ የሆነውን የቋንቋውን ሰዋስው ትምህርት ይዘት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዋሰው የአንድ ቋንቋ መሰረት ከሆነው ከድምጽ አንስቶ እስከ ሰፋፊ መዋቅር ድረስ የሚዘልቅ በመሆኑ ይህ ጥናትም የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅር ከያዘው ከሰዋስው ግምገማ መነሳት የተሻለ ነው ብሎ ስለታመነ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በክልል ደረጃ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም ላይ ነው፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማ ተብሎ ከተጠቀሱት መካከል መገምገም ላይ ነው::

## 1.2 አነሳሽ ምክንያት

መማሪያ መጻሕፍት ሲዘጋጁ፣ የትምህርት ይዘቶች ሲደራጁም ሆነ ሲመረጡ በልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ መሆን አለበት:: በመማሪያ መጻሕፍት የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ከክፍል ወደ ክፍል እንደ አዘጋጆቹ የትኩረት አቅጣጫ፣ የእውቀት ደረጃ፣ ልምድና ፍላጎት ሊሰፉ ወይም ሊጠብ አንዳንድ ጊዜ የራሳቸው የሆነ ክፍተቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡ በተለይ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮች በትምህርት ዓላማ ላይ አሉታዊ ተፅኖ ከማድረሳቸው በፊት ደግሞ ተከታታይ ግምገማ በማካሄድ ማሻሻል አስፈላጊ ነው:: ይህንን Cunningsworth (1984: 27) "አንድ መጽሐፍ ታትሞ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ በየጊዜው ግምገማና ክትትል መደረግ አለበት" በማለት ገልጸውታል:: ግምገማና ክትትል መደረጉ የይዘቶቹን ሙላትና ጉድለት በመለየት አስፈላጊ ማሻሻያዎችን ለማድረግ እንደሚያግዝም ጭምር ያስገነዝባሉ:: በመሆኑም ተመራማሪው ይህንን ጥናት እንዲያካሂድ የምሁሩ ሀሳብ አነሳስቶታል፡፡

ሌላው ደግሞ ከዚህ ቀደም በተለያየ ጊዜ የተለያዩ የሀገራችን የቋንቋ ምሁራን በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ዙሪያ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በቀረቡ መማሪያ መጻሕፍት ላይ በርካታ ጥናቶችና ግምገማዎች ማድረጋቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ለሆኑ 7ኛና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ምንም አይነት ጥናትም ሆነ ግምገማ ባለመደረጉ እና መማሪያ መጻሕፍት አዲስ እንደ መሆናቸው መጠን ሰዋስው የቋንቋው መሰረት ከሆነው ከድምጽ አንስቶ እስከ ሰፋፊ መዋቅር ድረስ የሚዘልቅ በመሆኑ ይህ ጥናትም የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅር ከያዘው ከሰዋስው ግምገማ መነሳት የተሻለ ሆኖ ስላገኘ አጥኚው ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ ምክንያት ሆኖታል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ

የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ሲሆን የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በመማሪያ መጽሐፍቱ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቀረቡበትን መንገድ መገምገም፤
2. በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት መፈተሽ፤
3. በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የታዩ ክፍተቶችንና የሚቃኑበትን መንገድ ማመልከት፣
4. መማሪያ መጻሕፍቱ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ተዛምዶ መፈተሽ የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከቋንቋ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማዎች መካከል አንዱ የስነ-ልሳን እውቀትን ማጎልበት ነው፡፡ ይህ ጥቅል ዓላማ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያየ መንገድ ተጽፎ ቀርቧል፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡ ይዘቶች መካከል ደግሞ ሰዋስው አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ማጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎችን ያስገኛል፡፡

1. ጥናቱ ትኩረት ባደረጉባቸው መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት፤ ጠንካራ ጎኖቹ የሚቀጥሉበትን እና ደካማ ጎኖቹ ደግሞ የሚሻሻሉበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡
2. የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ የተደራጁበትንና የቀረቡበትን መንገድ በመረዳት የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚመርጡበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡
3. ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው መማሪያ መጽሐፍት አዲስ ስራ ላይ እንደመዋላቸው፣ በመጻሕፍቱ ውስጥ በቀረቡ ሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ተጨማሪ ጥናት ለሚያደርግ አካል መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋሉ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ ነው፡፡ ለእርከኑ ክፍል ደረጃዎች “አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ” እና “አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ” በሚል ሁለት መማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ይህ ጥናት የሚያተኩረው “አማርኛን እንደ

ሁለተኛ ቋንቋ” በሚል በተዘጋጀው ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም አጥኚው በሚገኝበት አከባቢ ለእርከኑ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ቀርቦ እየተማሩ ያሉት መማሪያ መጻሕፍት አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚል የተዘጋጀው በመሆኑ ነው፡፡ በመጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ ይዘቶች ማለትም የቋንቋ ክሂል፣ የስነ-ጽሁፍ፣ እና የስነ-ልሳን እውቀት ዙሪያ የሚያተኩሩ ይዘቶች የተካተቱ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ጥናቱ የስነ-ልሳን ዘርፍ በሆነው በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ ምክንያቱም መማሪያ መጻሕፍት አዲስ እንደ መሆናቸው መጠን ሰፋ ያለ ጥናት ምርምር እንዲሁም ግምገማ የሚያስፈልግ ቢሆንም ካለው የጊዜ፣ የጉልበት፣ ገንዘብ ውስንነት እንጻር እና ሰዋስው የቋንቋው መሰረት ከሆነው ከድምጽ አንስቶ እስከ ሰፋፊ መዋቅር ድረስ የሚዘልቅ በመሆኑ ይህ ጥናትም የቋንቋውን መሰረታዊ መዋቅር ከያዘው ከሰዋስው ግምገማ መነሳት የተሻለ ሆኖ ስላገኘ በሰዋስው ላይ ብቻ ወስኖ ጥናቱን አካሂዷል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት

ሰለ መማር ማስተማር ስራ ሲነሳ ሁሌም ከጎን የማይጠፉ እና ሊለያዩ የማይችሉ የተማሪ መማሪያና የመምህሩ መምሪያ በመጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ Ur (1996: 183) "መማሪያ መጻሕፍት በአንድ ትምህርት አይነት ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን የትምህርት ይዘቶችን በውስጡ አቅፎ የሚይዝ ሲሆን የመምህሩ መምሪያ ደግሞ መምህሩም ሆነ ተማሪው ሊከተሉት የሚገባቸው መርህ የያዘ ሰነድ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከምሁሩ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው መማሪያ መጻሕፍት ባንድ ሀገር ውስጥ የሀገሪቱን ትምህርት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው መማር ያሉባቸው ይዘቶች የትኞቹ እንደሆኑ ተለይቶ የሚቀርብበትና በትምህርቱ ጊዜ መምህሩ እንዴት ማስተማር እንዳለበት፤ ተማሪዎች ደግሞ ለትምህርትነት የሚቀርበውን ይዘት እንዴት መማር እንዳሉባቸው የሚያሳይ ጠቋሚ የትምህርት መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል "የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተማሪው መማር ያለበት ጉዳይ (የትምህርት ይዘት) በተለያየ መንገድ የሚቀርብበት ሰነድ ነው" በማለት Grant (1987: 8) ይገልጻሉ፡፡ አስቀድሞ የቋንቋ ትምህርት ለተማሪው የሚቀርብበት የራሱ ዓላማ አለው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ይዘቶቹ ተደርድረው መምጣት ብቻ ሳይሆን የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የትምህርት ይዘቶች አቀራረብ፣ አጋዥና ደጋፊ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ተመርጠው እና ባንድ ላይ ተቀናጅተው በመማሪያ መጻሕፍት አማካኝነት ይቀርባሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪውም ሆነ መምህሩ በመማር ማስተማር ክንውን ውስጥ እንደ መሪ የተቀመጡ መመሪያዎችን በመከተል የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ስለሚያስችል መማሪያ መጻሕፍት የትምህርት መሪ ካርታ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

መማሪያ መጻሕፍት የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይዘቶቹ ተመርጠው ሲቀርቡም ሆነ ሲደራጅ የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ስለቋንቋው የሚያስቀምጠውን መርህ ተከትሎ መሆን አለበት (Grant, 1987: 8)፡፡ መርህን መሠረት ያደረገ ሲባል በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡፡

የመጀመሪያው መማሪያ መጻሕፍት የተማሪውን ዳራ ታሳቢ አድርገው መዘጋጀት እንዳለበት የሚገልጽ ሲሆን ይህም የተማሪውን ዕድሜ፣ ባህላዊ አኗኗር ሁኔታ ወይም ዳራ እና አካባቢያዊ

ሁኔታ ባጠቃላይ የተማሪውን ማህበራዊ አኗኗር ዘይቤ ታሳቢ አድርጎ መዘጋጀት እንዳለበት ነው። እነዚህ ጉዳዮች ታሳቢ መደረጋቸው ለተማሪው የሚቀርበው የትምህርት ይዘት ዕድሜያቸውን፣ አቅማቸውንና የአኗኗር ሁኔታቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መቅረብ እንዳለበት ስለሚፈለግ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ትምህርቱን ከመጡበት ማህበራዊ አኗኗር ጋር እያዛመዱ እንዲረዱ ያስችላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ የትምህርቱ ይዘት ተማሪዎች ከመጡበት ማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ ያፈነገጠ አይነት ከሆነ ያልኖሩበትን ባህል ለመቀበል ፍቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ። ከዚህ የተነሳ የትምህርቱ ዓላማ ግብ ላይመታ ስለሚችል ጥንቃቄ በተሞላ መንገድ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት።

ሁለተኛው ደግሞ የክፍል ደረጃ ነው። የሰው ልጅ እያደገ በሄደ ቁጥር የአዕምሮ ዕድገቱ በዚያው ልክ እያደገ ይመጣል። በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ አዕምሮ ቀድሞ ከለመዳቸው በተጨማሪ አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅና ለመልመድ ይፈልጋል። ይህ ደግሞ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ብቻ የሚከሰት ሳይሆን ወደትምህርቱ ዓለም ሲመጣም ተማሪዎች ከአንድ ክፍል ደረጃ ወደሌላ ክፍል ደረጃ ሲሸጋገሩ ቀድመው ከተማሩት የትምህርት ይዘት በተጨማሪ አዲስ ነገር እንዲቀርብላቸው ይፈልጋሉ። ቀድሞ የተማሩት የትምህርት ይዘት ቢኖር እንኳን ከቀድሞው አቀራረብ ስልት ለየት ባለመልኩ ሰፍቶ እንዲቀርብ ይፈልጋሉ። ስለሆነም የሚቀርበው የትምህርት ይዘትም እየሰፋ መሄድ አለበት። ይህ ሲባል ካሉበት የክፍል ደረጃ በላይ መሆንም የለበትም። ለተማሪዎች የሚቀርበው ትምህርት ይዘት ከችሎታቸው (ከእውቀታቸው) በላይ ከሆነ የቀረበውን የትምህርት ይዘት ከማወቅና ከመለየት ይልቅ ጉዳዩን በደንብ ሳይለዩ ያልፋሉ። በሌላ በኩል ለተማሪዎች የሚቀርበው የትምህርት ይዘት ከአቅማቸው በታች ከሆነ አዕምሯቸው አዲስ ነገር ላያገኝ ይችላል። ስለዚህ የሚቀርበው የትምህርት ይዘት አቅማቸውን፣ እውቀታቸውንና ችሎታቸውን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ስለሚታሰብ ነው። በዚህን ጊዜ ትምህርቱ ዓላማውን ወይም ግቡን ሊሲት ይችላል።

መማሪያ መጻሕፍት በአይነት የተለያየ እንደሆኑ የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ። እንደ Grant (1987: 12) የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ስርዓት ተኮር ወይም ሰዋሰው ተኮር እና ተግባቦታዊ ተኮር በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል። ስርዓተ ተኮር መማሪያ መጻሕፍት ተማሪው የታላሚ ቋንቋ ስርዓት እንዲማር የሚቀርብ ሲሆን ለቋንቋው ቅርፅና ሰዋስው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ መማሪያ መጻሕፍት አይነት ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ቀደም ባሉት ዘመናት መማሪያ መጽሐፉ በቋንቋው ሰዋስዋዊ ቅርጽ ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑን ነው። ቀደም ባሉት ዘመናት ራሳቸውን የቻሉ መማሪያ መጻሕፍት ሆነው የሚዘጋጁት ባሁኑ

ሰዓት ባንድ ቋንቋ መማሪያ መጽሕፍት ውስጥ እንደ አንድ ትምህርት ይዘት ይቀርቡ የነበሩ ይዘቶች ማለትም በውጤት ተኮር ዘዴ የሚቀርበውን ሰዋስው ይዘትን የሚያቅፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በሁለቱም የሚደራጁ ሰዋስው ይዘቶች ትኩረታቸው በቋንቋው ቅርጽ ላይ በመሆኑ ነው፡፡

ሌላኛው ተግባቦታዊ መማሪያ መጽሐፍ ሲሆን ቋንቋውን በተለያዩ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ለተግባቦታዊ ብቃት መጠቀምን ትኩረት ያደረገ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ መማሪያ መጽሐፉ ከቋንቋው ቅርፅ ይልቅ ቋንቋውን ለተግባቦት ተግባር መጠቀምን እና ተማሪዎች በቋንቋው አማካኝነት ስሜታቸውንና ፊላጎታቸውን እንዲያንፀባርቁ ለማስቻል የሚያግዝ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህም እንደቀደሙት ሁሉ ራሳቸውን የቻሉ መማሪያ መጻሕፍት ሆነው የሚዘጋጁት ባሁኑ ሰዓት ባንድ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ እንደ አንድ ትምህርት ይዘት ይቀርቡ የነበሩ ይዘቶች ማለትም በሂደት ተኮር ዘዴ የሚቀርበውን ሰዋስው ይዘትን የሚያቅፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በሁለቱም የሚደራጁ ሰዋስው ይዘቶች ትኩረታቸው የቋንቋውን ንዕስ ይዘቶችን ለተግባቦት ተግባር ማዋል ላይ የሚያተኩሩ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩል Dawson (1984)ን ጠቅሰው ሰሚራ (2010: 13) “መማሪያ መጻሕፍት መዋቅራዊ፣ ሁኔታዊና አገልግሎታዊ” ተብለው በሶስት እንደሚከፈል በጥናታቸው አንስተዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው መማሪያ መጻሕፍቱ እንደሚሰጡት አገልግሎት የተለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ በዚህ መሰረት መዋቅራዊ መማሪያ መጻሕፍት በቋንቋው ቃላት፣ ሀረጋትና አረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ሁኔታዊ መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍቱ የሚቀርቡ ይዘቶች በብዛት አዳዲስ ይዘቶች በየጊዜው ለተማሪዎች በማቅረብ ካለፉት ይልቅ አዳዲሶቹን ይዘቶች እንዲለምዱ የሚያደርጉ መማሪያ መጻሕፍት መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በመጨረሻም አገልግሎታዊ መማሪያ መጻሕፍት ተማሪዎች ከቋንቋ ትምህርት የሚገኘውን እውቀት ለተግባቦታዊ አገልግሎት እንዲያውል የሚያደርግ መማሪያ መጻሕፍት መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በሌላ በኩል Grant (1987)፣ ሰሚራ (2010) እና ዘላለም (1998) ስለመማሪያ መጻሕፍት አይነቶች የተደረገውን አከፋፈል ሲያብራሩ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የሚያደርጋቸውን ጉዳዮች ባቀፈ መልኩ ሲሆን አከፋፈሉም እንደምሁራኑ የብያኔ ልዩነት ያለው መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡

ሌላው Ur (1996)ን፣ Mc Donough (1990)ን እና Cunningsworth (1984)ን ጠቅሰው ዘላለም (1998: 23-24) "የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ግልጋሎታዊ /ሀሳባዊ/፣ መዋቅራዊ /ሰዋሰዋዊ/፣ ርዕስ ተኮር፣ ክሂል ተኮር እና ሁኔታዊ ተብሎ በአምስት ይከፈላሉ" በማለት ይገልጻሉ። ከላይ ከቀረበው መረዳት የሚቻለው መማሪያ መጻሕፍት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለተማሪው ከሚቀርብበት መሳሪያ አንዱ ሲሆን ይዘቶቹ የትምህርቱን መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካት ከትምህርቱ ዓላማ አንጻር የተቃኙ መሆን አለባቸው። ከቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ዓላማዎች መካከል አንዱ ደግሞ ተማሪው የሥነ-ልሳን እውቀት እንዲኖረው ማስቻል ሲሆን ይህ አብይ የቋንቋ ዓላማ በውስጡ የተለያዩ ይዘቶችን አካቶ ከሚይዘው መካከል አንዱ ሰዋስው ነው። ቀደም ባሉት ዘመናት ሰዋስው ከሚቀርብበት መማሪያ መጻሕፍት አይነቶች መካከል ተግባቦታዊ፣ ስርዓተ ተኮር፣ መዋቅራዊ (ስዋስዋዊ) የሚባሉት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት የቋንቋውን ሰዋስው ህጎችን ለተማሪው እንደትኩረት አቅጣጫቸው ይዘቶቹ የሚዋቀሩበትና የሚቀርቡበት ነው። እነዚህን መጻሕፍት በዘመናዊ ትምህርት ውስጥ በቀጥታ ባናገኛቸውም ነገር ግን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሚቀርቡበትና ከሚደራጁበት ዘዴዎች ውስጥ እናገኛቹዋለን። ለምሳሌ ተግባቦታዊ መማሪያ መጻሕፍት የሰዋስው ይዘትን ተግባቦታዊ በሆነ መልኩ የሚያቀርብ በመሆኑ ሂደት ተኮር የቋንቋ አቀራረብ ዘዴ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሥርዓተ ተኮር መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ በቋንቋው ቅርጽ ላይ በማተኮሩ ከውጤት ተኮር አቀራረብ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው ማለት ይቻላል። መዋቅራዊ (ሰዋስዋዊ) መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ በቋንቋው ፍች ሥርዓት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ውጤት ተኮር ዘዴ ጋር የሚመሳሰል ነው። በመሆኑም እነዚህ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከሰዋስው አቀራረብና አደረጃጀት ዘዴዎች ጋር ተቀራራቢ በመሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ ተካተዋል።

## 2.2 ሰዋስውና የሰዋስው ትምህርት

በተለያዩ ዘመናት በሰዋስው ዙሪያ ሀገር በቀልና ውጪ ሀገር የቋንቋ ምሁራን በርካታ ጥናቶች ቢያካሂዱም አንድ ወጥ ብያኔ ማግኘት መስጠት አልቻሉም። ለዚህ ደግሞ እንደምክንያት (ጌታሁን 1990: iv) "ሰዋስው በራሱ ፅንሰ ሀሳባዊ አሻሚነት ያለው መሆኑን" ይገልፃሉ። ይህ ማለት ሰዋስው ባንድ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ብቻ ሳይሆን ውስብስብ በሆኑ የቋንቋ ስርዓቶች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው። በሌላ በኩል Stern (1983: 131) ለሰዋስው ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት የመስኩ ምሁራን የትኩረት አቅጣጫ መለያየት አስቸጋሪ እንዳደረገው ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ Brown (1994: 45) "ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት ነው" በማለት ባጭሩ ይገልጻሉ። ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ሰዋስው ሲባል የአንድ ቋንቋ መሰረት ከሆነው

ከድምጽ አንስቶ ቋንቋው በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ያለውን አገልግሎት ድረስ ያለውን ሰፊ መዋቅር የሚመለከት መሆኑን ያመላክታል፡፡ ድምጽ በሥርዓት ተቀናጅቶ ቃላትን፤ ቃላት በሥርዓት ተቀናጅቶ ሀረግን፤ ሀረጋት በሥርዓት ተቀናጅቶ አረፍተ ነገርንና እነዚህ አረፍተ ነገሮች ደግሞ በቋንቋው ተጠቃሚ ማህበረሰብ ዘንድ የሚኖረውን ትክክለኛውን አጠቃቀም ሂደትን የሚመለከት መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ሲባል የቋንቋው ተጠቃሚ ማንኛውም ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ በቋንቋው እየተገለገለ እያለ ከቋንቋው ትክክለኛ አጠቃቀም ሂደት ወይም አነጋገር ሥርዓት ቢወጣ (ቢሳሳት) ስህተቱንና እንደት መስተካከል እንዳለበት አጠቃላይ ሥርዓቱን የሚመለከት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ባየ (2000:10) "ሰዋስው የአንድ ቋንቋ ከድምፅ አሰካክ እስከ ሀረግ ምስረታ ድረስ የሚያጠና ነው" የሚል ድምዳሜ ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚህ ብያኔ መረዳት የሚቻለው ሰዋስው የአንድ ቋንቋ መሰረት የሆነው ድምጽ በስርዓት ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው ሀረጋትን እና ሀረጋት ሲቀናጁ በመጨረሻ የሚያስገኙትን ዓረፍተ ነገር ድረስ ያለውን ስርዓት የሚመለከት መሆኑን ነው፡፡ በዚህም ሂደት የቋንቋው ስርዓት ማወቅ ብቻ ሳይሆን የቋንቋው ተናጋሪዎች በአጠቃቀም ጊዜ ቋንቋው "ሰዋስዋዊ ነው (ትክክለኛ ነው)" አልያም "ስህተት ነው" ለማለት የሚያስችለውን ምክንያት ጭምር ማወቅን የሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ሰዋስው ከድምፅ አቀነጃጀት እስከ ዓረፍተ ነገር አወቃቀር ድረስ ያለውን የሚመልከት ብቻ ሳይሆን ቋንቋው በሚነገርበት አከባቢ ትክክለኛውን የአነጋገር ስርዓት ጠብቆ መነገር አለመነገሩን ለይቶ መጠቀም መቻሉን የሚያሳይ ነው:: ማለትም ተናጋሪው እየተናገረ እያለ ወይም ሌሎች እየተናገሩ ብሳሳቱ እንኳን ስህተታቸውን ከነምክንያቱ ማወቅን የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን የሚገልፅ ሀሳብ ነው::

ከላይ ከተነሳው ሀሳብ ቀደም ባሉት ዘመናት ሰዋስው ከድምፅ አስከ ሀረግ አወቃቀር ድረስ ያለውን የሚመለከት ነበር ማለት ይቻላል:: ይህ ደግሞ ሰዋስው በአወቃቀር ስርዓት ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው ወደሚል ድምዳሜ ይወስደናል:: በዘመናዊ መንገድ የቀረቡ የሰዋስው ጥናቶችና የትምህርት ይዘቶች ግን ሰዋስው ከድምፅ አፈጣጠር እስከ ውስብስብ ዓ.ነገር አወቃቀርን ከሚነገርበት (ከሚቀርብበት) አውድ ጭምር የሚይዝ መሆኑን አስመስክረዋል (ባየ 2002: 13):: አያይዘውም "የአማርኛ ሰዋስው ሲባል የቋንቋው ድምፀ-ልሳናት አይነት፣ አፈጣጠርና አቀነጃጀት፤ የቃል ክፍል አፈጣጠርና አቀነጃጀት፤ የሀረጋቱ አይነትና አወቃቀር፤ እንዲሁም የዓ.ነገር አይነትና አወቃቀር ወይም አቀነጃጀት ስርዓት የሚመለከት ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ሰዋስው የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በዘመናዊው አስተሳሰብ በሀረግና በዓረፍተ ነገር ላይ ብቻ ሳይወሰን የቋንቋ መሠረት ከሆነ ከትንሹ ድምፅ ጀምሮ እስከ ሰፋፊ አረፍተ ነገር መዋቅር ድረስ ያለውን የሚመለከት ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። ይህም ድምፆች በስርዓት ተቀናጅተው ቃልን የሚያስገኙበትንና እነዚህ ቃላት ደግሞ የሚፈቱበት ስርዓትን፤ ቃላቱ በስርዓት ተቀናጅተው ሀረግን፤ ሐረጎች እንደዛው በወጉ ተዋቅረው አረፍተ ነገር የሚያስገኙበትን አጠቃላይ ስርዓት የያዘ ነው። ስለሆነም ሰዋስው የቋንቋውን አወቃቀር፣ ፍችና አጠቃቀም ስርዓት የያዘ ነው ማለት ይቻላል።

በመሆኑም ሰዋስው ስርዓታዊ የድምፆች ቅንጅትን፣ የቃላት አቀነጻጀትና ፍች ስርዓትን፣ የሐረጋትና አረፍተ ነገሮች አቀነጃጀትን ሁሉ የሚያጠቃልል ሆኖ፤ እነዚህ እርስ በርሳቸው እየተቀናጁ ደረጃ በደረጃ የሚቀርቡበትን ከነአጠቃቀም ስርዓት የሚይዝ ነው ማለት ይቻላል። ጠቅለል ባለ አገላለጽ ሰዋስው በስነ-ድምፅ፣ በስነ-ምዕላድ፣ በስነ-ሀረግ፣ በአረፍተ ነገርና በስነ-ፍች ላይ የሚያተኩር ጽንሰ ሀሳብ ነው ማለት ይቻላል። በመሆኑም ጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ 7ኛና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ በሰዋስው ዙሪያ የሚያተኩሩ ይዘቶች እነዚህን ጉዳዮች ይዘው መቅረባቸውንና መደራጀታቸውን ግምገማ ተደርገዋል።

## 2.3 የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

ባንድ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ተማሪዎች ይገኛሉ። እነዚህ ተማሪዎች የሚቀርበውን ትምህርት የሚቀበሉበት የአቀባበል ደረጃቸውም የተለያየ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለትምህርትነት የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቱም የተለያየ ሆኖ እናገኛለን። ይዘቶቹ ደግሞ ባንድ አይነት መንገድ ሳይሆኑ በተለያየ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ። ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ የተማሪውን ዳራ፣ የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፤ የይዘቶቹን መለያየት መሰረት አድርጎ እንዲሁም የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በተለያየ መንገድ መቅረብ አለበት። ከሰዋስው ትምህርት ጋር ተያይዞ ከሚነሱ የአቀራረብ መንገዶች በዚህ ጥናት ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ሂደት ተኮር እና ውጤት ተኮር የተባሉት ተካተዋል።

### 2.3.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

በዚህ አቀራረብ ስልት በመጀመሪያ ለትምህርትነት በተመረጡ ሰዋስው ይዘቶች ዙሪያ ማብራሪያና ትንታኔ ይቀርብና ቀጥሎ ምሳሌዎች ይሰራሉ፤ በመጨረሻም ተማሪዎች የቀረበውን ማብራሪያ፣ ትንታኔና ምሳሌ መሰረት በማድርግ ሌሎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያስችል አቀራረብ ስልት መሆኑን (Cunningsworth, 1995: 8)፣ (Harmer, 1987: 9) እና (Larsen-freeman, 1991: 151) ይገልፃሉ።

ከላይ ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለተማሪዎች በትምህርትነት ሊቀርቡ በተለዩ ሰዋስው ይዘቶች ዙሪያ ጽንሰ ሀሳባዊ ገለጻ እና ማብራሪያ በምሳሌ ታግዞ ይቀርብና በቀረበው ምሳሌና ማብራሪያ መሰረት ሌሎች መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚደረግ አቀራረብ መንገድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ገለፃ ተሰጥቶ የሚቀርብ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ስለይዘቶቹ በቀላሉ ለማሳወቅ ምቹ ዘዴ መሆኑ የሚታመን ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሌም ለተማሪዎች ገለፃና ማብራሪያ ቀርቦ ስርዓቱን መማራቸው የመማር ሂደቱን አስቸጋሪ ሊያደርግ እንደሚችል ምሁራኑ ያስቀምጣሉ፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት ደግሞ ተማሪዎች ስለይዘቶቹ ከራሳቸው ሀሳብ አፍልቀው እንዳይረዱ ስለሚገድብ፤ ከዚህ የተነሳ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነትና ተሳትፎ የሚቀንስ መሆኑ፣ እንዲሁም ገለፃው በተግባቦት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ቶሎ እንዲረሱ ስለሚያስችል ነው የሚል አንድምታ አለው፡፡

### 2.3.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

በዚህ ስልት የሚቀርብ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አስቀድሞ በተመረጡ ሰዋስው ይዘቶች ዙሪያ ምሳሌዎች ይቀርብና በምሳሌዎች እየተመሩ መልመጃዎችን በመስራት በራሳቸው ጥረት የቋንቋውን ስርዓት ለይተው እንዲገነዘቡ የሚያስችል አካሄድ ነው በማለት (Woods, 1995: 75) ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ለትምህርትነት በሚቀርበው ሰዋስው ይዘት ዙሪያ ምሳሌዎች፣ አስረጂዎች፣ ማሳያዎች፣ ወዘተ ዝርዝር መረጃዎች ይቀርቡና በምሳሌዎቹ መሪነት ታላሚውን ንዑስ የቋንቋ ዓላማን ለማሳካት የሚቀርብ ነው፡፡ አቀራረብ ስልቱም ተማሪዎች ከቋንቋው ዝርዝር ህግ ተነስተው አጠቃላይ ወደሆነው እንዲሸጋገሩ ያስችላቸዋል፡፡

### 2.3.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ

እንደ Batstone (1994: 51) ገለፃ ውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በታላሚ ቋንቋ ሰዋስው ስርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የዓ.ነገር አመሰራረት እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያግዝ ዘዴ ነው፡፡ ስሙ እንደሚያመላክተው በዚህ ስልት የሚቀርብ ሰዋስው ይዘትን ተማሪዎች አስቀድመው በተለያየ መንገድ እንዲረዱ ይደረግና ከትምህርቱ ያገኙትን ዘርዝረው እንዲያሳዩ የሚደረግ ስልት ነው፡፡

በመሆኑም ዘዴው የሰዋስው አሃዶችን ለብቻቸው በመተንተን በቋንቋው ስርዓት ላይ ተመስርቶ ትክክለኛ ዓ.ነገሮችን ለመመስረት ያስችላቸዋል፡፡ በሌላ ጎኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው እንዲመድቡ፣ ቃላትን፣ ሀረጋትን፣ ዓ.ነገሮችን በተናጠል እንዲተነትኑ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ በአጠቃላይ በቋንቋው ቅርጽ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ጥናቱም በውጤት ተኮር

አቀራረብ ዘዴ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መኖሩን ከመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ለይቶ ግምገማ አቅርቧል።

### 2.3.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ

የሰዋሰው ይዘቶችን በአውድ ውስጥ በማምጣት ለመስተጋብራዊ አግልጋሎት የሚያውል ዘዴ ነው (ሰሚራ 2010: 10)። ዓላማውም ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋል ነው። በውጤት ተኮር የሚቀርብ ሰዋስው ትምህርት ይዘት ቅርፅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን በሂደት ተኮር ዘዴ የሚቀርበው ሰዋስው ትምህርት ደግሞ ለተግባቦታዊ አገልግሎት የሚውል መሆኑን ያስገነዝባሉ። ስለሆነም ዘዴው ሙሉ ለሙሉ ከውጤት ተኮር አቀራረብ የተለየ መሆኑን በዚህ ማወቅ ይቻላል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ በዚህ አቀራረብ ዘዴ ወይም ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገምግመዋል።

ከላይ የተመለከትናቸው የአቀራረብ ስልቶች ፍጹም ናቸው ማለት አይደሉም። ሁሉም የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ያሏቸው ናቸው። ለአብነት ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር አቀራረብን ብንመለከት፤ ዉጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የአንድን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት (የቋንቋውን ቅርጽ) የሚያሳዉቅ ሲሆን ለመዋቅሩ ፍቺና አዉዳዊ አጠቃቀም የሚሰጠዉ ትኩረት አናሳ መሆኑ አቀራረቡን የተጓደለ ያደርገዋል። ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚዉን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍቺና አዉዳዊ አጠቃቀም ተገንዝበዉ በቋንቋዉ መገልገል እንዲችሉ ማድረጉ አዎንታዊ ገጽታዉን ቢያሳይም ሰዋስውን በቀጥታ ማቅረብ ያለመቻሉ ደግሞ የድክመቱ መገለጫ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ሁለቱንም አቀራረቦች አቀናጅቶ ማቅረቡ የሰዋስው ትምህርት ቅርጽና አጠቃቀም መንገድ በቅንጅት አዉቆ ለመገልገል ስለሚረዳ የአቀራረብ ስልቶችን አንዱ የሌላውን ክፍተት ሊሸፍን በሚችል መልኩ እያፈራረቁ ወይም እያዋሀዱ መጠቀም ጠቀሜታው የጎላ ነው።

## 2.4. የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚደራጁ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተማሪውን አጠቃላይ ዳራ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት። የተለያዩ ምሁራን የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት አስመልክቶ የየራሳቸውን ሀሳብ ያስቀምጣሉ። ከእነዚህ ምሁራን መካከል Tayler (1949) እና Taba (1962) የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነት ጠብቀው መደራጀት እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ። ተዋረዳዊ ግንኙነት ሲባል በተለያየ ክፍል ደረጃዎች የሚካተቱ ሰዋስው

የትምህርት ይዘቶች እርስ በራስ ግንኙነትን ጠብቀው መደራጀት እንዳሉባቸው የሚያሳይ ሲሆን ጎናዊ ግንኙነት ደግሞ ለአንድ ክፍል ደረጃ በተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎችና ርዕሰ ጉዳዮች ስር ያላቸውን ግንኙነት ጠብቀው መደራጀት እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም ይዘቶቹ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ኖሯቸው መደራጀት እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.4.1 ተከታታይነት (Continuity)

እንደ (Tayler, 1949: 84) ተከታታይነት ተማሪው የቀረበውን ሰዋስው ይዘት ይበልጥ እንዲረዳው ለአንድ ክፍል ደረጃ በተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ምዕራፎችና አውዶች ውስጥ ተደጋግመው የሚቀርቡበት ሂደት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ መማሪያ መጽሐፉ ኢ-አፍ ፊት ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጁ እንደመሆናቸው መጠን ለትምህርትነት የተመረጡ ይዘቶች ተከታትለው መቅረብ ተማሪዎች ይዘቱን በሚገባ እንዲረዱት፣ ለይተው እንዲያውቁትና በተገቢው ሁኔታ ለማህበራዊ መስተጋብር ወይም ለተግባቦት እንዲያውሉት ስለሚያስችል፤ እንዲሁም አሻሚና ውስብስብ የሆኑ ሰዋስዋዊ ቅርጾችን በቀላሉ ለመረዳት ስለሚያግዝ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት በናሙናነት በተመረጡ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት ባለው መንገድ መጀራጀቱ ተገምግሟል፡፡

### 2.4.2 ተለጣጣቂነት (Sequence)

ተለጣጣቂነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ለተማሪው በተዘጋጀ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታትለው በመቅረብ ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ እንዲሁም ቀድሞ ከቀረበው መንገድ ቀጥሎ የሚቀርበው ለየት ብሎ የሚመጣ መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ Larsen-freeman (1991) ተለጣጣቂነት በመማሪያ መጻሕፍቱ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ተዋረዳዊ አደረጃጀት የሚመለከት ሲሆን ይህም በተከታታይ የክፍል ደረጃ ይሁን ምዕራፎች ውስጥ የሚደራጁ የትምህርት ይዘቶች ተዋረዳዊ በሆነ መንገድ መቀናጀት እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ፡፡ የአንድ ትምህርት ይዘት መነሳት ሌላ ተዛማጅ የሆነ ጉዳይ እንዲነሳ ማድረጉ አይቀርም፡፡ እነዚያ ይዘቶች ደግሞ እርስ በርሳቸው ዝምድና ያላቸውና የሚደጋገፉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍቱ ሲደራጁ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ሳይሆን ቀድሞ ከመጣው ቀጥሎ የሚመጣው ራሱን ሳይደግምና ሳብነቱን ሳይለቅ ለየት ባለመንገድ መደራጀቱን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ተለጣጣቂነት ተቀራራቢና ተደጋጋፊ የሆኑ ይዘቶች የተማሪውን እውቀት ለማስፋት በተለያያ ስልት የሚደራጅበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡ ጥናቱ

ተተኳሪ ባደረገባቸው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መመሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ጠብቀው መደራጀቱን ገምግሟል።

## 2.5 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶች እንደ ሁኔታው ዳሰሳ ተደርገዋል። ቀደምት ስራዎቹ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (ከ5ኛ- 8ኛ ክፍል) ላሉት የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብን የሚገመግሙ እንደመሆናቸው ባይነት ባይነታቸው ተዳስሰዋል።

ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ግምገማ ካደረጉት ጥናቶች መካከል የተስፋዬ(1993)፣ ባዩ(2004)፣ ጌታሁን(2007)፣ ሰሚራ(2010)፣ ፈለቀች(2014) እና ሐዋዝ (2000) ተጠቃሾች ናቸው። ከእነዚህ መካከል የተስፋዬ(1993)፣ ባዬ(2004)፣ ሰሚራ(2010) እና ፈለቀች(2014) አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ለሆኑ ተማሪዎች በተዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን የጌታሁን(2016) እና ሐዋዝ(2000) አማርኛ አፍ-ፈት ለሆኑት ተማሪዎች በተዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። ጥናቶቹ በየክልሎቹ ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ በዋሉት ተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ በቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ያተኮሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ የአቀራረብ ዘዴያቸውና የምርምር አካሄዳቸው የሚመሳሰሉ ናቸው።

ከዚህ ጥናት ጋር የጠበቀ ዝምድና አለው ከሚባለው የተስፋዬ(1993) "በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ የተጠናው ስራ ተጠቃሽ ነው። የተስፋዬ ጥናት ትኩረት ያደረገው በሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ነው። የመጀመሪያው በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ መልመጃዎች ለቋንቋው ቅርፃዊ ስርዓትና ፍች ትኩረት መስጠት አለመስጠታቸውን የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመልመጃዎች አደረጃጀት ምን ይመስላል? የሚሉ ናቸው። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ በናሙናነት ከተመረጠው መማሪያ መጽሐፍ በሰነድ ፍተሻ እና 8ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ ቃለ-መጠይቅ በመጠቀም መረጃዎችን አደራጅቶ ትንተና አካሂዷል። በውጤቱም የሰዋስው ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከግንዛቤ-ተኮር ወደ ማዋቀር-ተኮር የአደረጃጀት ስልቶችን ተከትሎ መደራጀቱን አስቀምጧል። በእነዚህ ስልቶች የተደራጁ

የሰዋስው ይዘቶችና መልመጃዎች ለታላሚው ቋንቋ ቅርፃዊ ስርዓትና ፍቺው ሚዛናዊ ትኩረት ያልሰጡ፤ ይዘቶቹ ከጥቅል ሰዋስው ባህሪይ ወደ ዝርዝር ሰዋስው ባህሪይ ያልተደራጁ፣ እንዲሁም ለገለጻዊና ኢ-ገለጻዊ አደረጃጀት ስልት ሚዛናዊ ትኩረት ያልሰጡ መሆናቸውን እንደ ችግር አንስቷቸዋል። በመጨረሻም ጠንካራ ጎኖቹም የሚበረታቱበትን፤ የታዩ ደካማ ጎኖች ደግሞ የሚሻሻሉበትን የመፍትሔ አቅጣጫ በመጠቆም አቅርቧል።

ምንም እንኳን የተስፋዬ ጥናት በተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለሰዋስዋዊ ቅርጽ እና ፍች ትኩረት መስጠት አለመስጠቱን እና የሰዋስው ይዘቶች አደረጃጀቱ ምን መልክ እንዳለው የሚገመግም ቢሆንም ይህ ጥናት የሰዋስው ይዘቶች ለሰዋስዋዊ ቅርጽ እና ፍች በተጨማሪ ለአገባብ፣ ለቃላትና አያያዥ፣ ወዘተ ትኩረት መስጠት አለመስጠቱን፤ የሰዋስው ይዘቶች ከየት ወደት እንደቀረቡ እና የተደራጁበትን መንገድ የሚፈትሽ ነው።

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው የሰሚራ(2010) "በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጃት ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፋቸው ያቀረቡት ጥናት ተጠቃሽ ነው። ጥናቱ ሰነድ ፍተሻን ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ያዋለ ሲሆን መረጃዎች በተገኙበት ሁኔታ አይነታዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም በገላጭ ስልት ትንተና አቅርቧል። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመላክተው በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ይልቅ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ ይዘቶች አብላጫውን የሚሸፍን ቢሆንም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይም ሆነ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረበው ይዘት በተሻለ ሁኔታ መቅረቡን አመልክተዋል። ከውጤት ተኮር ይልቅ ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንደዋለ፤ ከአደረጃጀት አንፃርም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ተከታታይነት ኖሯቸው የተደራጁና ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ መሄዱን ጠቁመዋል። በጥናቱ በአንድ ትዕዛዝ ስር የተለያዩ ሶስትና ከዚያ በላይ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ታጭቀው መቅረቡና ትዕዛዞቹ ግልፅ ሆነው ከመቅረብ ይልቅ አሻሚነት ያሉባቸው መሆኑ እንደ ደካማ ጎን አንስተዋል። በመጨረሻም ጥናቱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለተስተዋሉ ደካማ ጎኖች ማሻሻያ መፍትሔ ሀሳብ ነው ያሏቸውን ነጥቦች በመጥቀስ አጠቃለዋል። የሰሚራ ጥናት በርዕሰ ጉዳይ፣ በአጠናን ዘዴ፣ በክልል ምርጫ፣ ወዘተ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም መማሪያ መጽሐፉ ስራ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ የተጠና

መሆኑ፤ ጥናቱ ተተኳሪ ባደረገው ክፍል ደረጃ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ አዲስ ስራ ላይ በዋሉ መማሪያ መጻሕፍት ላይ እና የሰዋስው ይዘቶች ተለጣጣቂነት ለመፈተሽ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት በጥምር መጠቀሙ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ባዩ (2004) "በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ" በሚል ርዕስ የቀረበው ሌላኛው ተጠቃሽ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በመማሪያ መጽሐፎቹ ውስጥ የቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ ከግልጽኝነት፣ ከትክክለኛነት፣ ከተመጣጣኝነት እና ከተገቢነት አንጻር፤ የይዘቶቹን አደረጃጀት ደግሞ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አንጻር ፈትሸዋል፡፡ መረጃዎቹ ከእርከኑ መማሪያ መጽሐፍት በሰነድ ፍተሻና በናሙናነት ከተመረጡ ተማሪዎችና መምህራን በጽሁፍ መጠይቅ፤ እንዲሁም ከመጽሐፍቱ አዘጋጆች ቃለ-መጠይቅን በመጠቀም ተሰብስበው አይነታዊ ወይም ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡ በውጤቱም በእርከኑ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ችግሮች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ለአብነት በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚቀርቡ ገለፃዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትዕዛዞችና ጥያቄዎች ተማሪዎችን የሚያደናግሩ መሆኑን፤ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ተመጣጣኝነት ወይም ሚዛናዊነት የጎደለው መሆኑን፤ ለስነ-ድምፅ ዝቅተኛ ትኩረት መስጠቱን፣ ደረጃ መጣኝ አለመሆኑን እና ይዘቶቹ መርሃ-ትምህርትን መሰረት ያላደረጉ በመሆኑ የተገቢነት ችግር፣ ወዘተ ጎልቶ እንደሚንፀባርቅበት አመልክቷል፡፡ በመጨረሻም መፍትሔ ሀሳብ ይሆናሉ ብሎ ያመኑባቸውን ሀሳቦችን ጠቅሶ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡ የባዩ ጥናት በርዕሰ ጉዳይ፣ በአጠናን ዘዴ፣ በክልል ምርጫ፣ ወዘተ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም መማሪያ መጽሐፉ ሰፊ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ የተጠና መሆኑ፤ ጥናቱም ተተኳሪ ባደረገው የክፍል ደረጃ፣ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት የገመገመበት መንገድ፣ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ልዩነት

ፈለቀች(2014) “በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ” በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተጠናው ስራ ሌላኛው ተጠቃሽ ነው፡፡ ጥናቱ የሰዋስው ይዘቶችን አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ውጤት ተኮር እና ሂደት አንጻር፤ አደረጃጀቱን ደግሞ ከተከታታይነትና ከተለጣጣቂነት አንጻር ገምግሟል፡፡ ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተጠቅመዋል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ገላጭ ምርምር ዘዴ የተመረጠ ሲሆን የተገኘው መረጃ በአይነታዊ መንገድ

ተተንትኑዋል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረበ ይዘት አለመኖሩን፣ በውጤት ተኮር ዘዴ ከቀረበው ይልቅ ሂዴት ተኮር በሆነ መንገድ የቀረበው አብላጫውን ድርሻ መያዙን፤ ምንም እንኳን ይዘቶቹ በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመው ቢደራጁም ያለ ብስለት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ስፋትና ጥልቀት ሳይጨምር፤ የአደረጃጀት መንገድ ሳይለውጥ መደራጀቱን ጠቁመዋል። በተተኳሪ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች የአቀራረብና አደረጃጀት መርሆችን ባካተተ መልኩ በምሳሌ ታግዘው መቅረባቸው፣ ተከታታይነትን አግኝተው መደራጀቱ እንደ ጠንካራ ጎን ታይቷል። አብዛኛዎች ይዘቶች ጥልቀታቸውን ሳይጨምሩ መደራጀቱ ደግሞ እንደ ደካማ ጎን ተነስተዋል። በመጨረሻም የታዩ ደካማ ጎኖች የሚሻሻሉበትን መፍትሔ ሀሳብ በመጠቆም ጥናታቸውን አጠናቅቀዋል። የፈለቀች ጥናት በርዕሰ ጉዳይ፣ በአጠናን ዘዴ፣ በክልል ምርጫ፣ ወዘተ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም መማሪያ መጽሐፉ ሰፊ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ የተጠና መሆኑ እና ጥናቱ ተተኳሪ ባደረገው ክፍል ደረጃ ልዩነት መኖሩን ያሳያል። ይህ ጥናት ደግሞ አዲስ ስራ ላይ በዋሉ መማሪያ መጻሕፍት ላይ እና የሰዋስው ይዘቶች ተለጣጣቂነት ለመፈተሽ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት በጥምር መጠቀሙ ልዩ ያደርገዋል።

ጌታሁን(2007) "የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ናሙናነት" በሚል ርዕስ ያጠኑት ሌላኛው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው ስራ ነው። ጥናቱ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን እንደ አፍ መፍቻ ተዘጋጅተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ባሉት የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የስነ-ልስን እውቀት ዘርፍ በሆነው በቋንቋው የሰዋስው ትምህርት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን፤ ሰነድ ፍተሻን የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ፤ እንዲሁም ጽሁፍ መጠይቅን በደጋፊነት ተጠቅመው መረጃዎች ተሰብስቧል። በውጤቱም የእርከኑ መማሪያ መጽሐፍት ከይዘት አደረጃጀት አንፃር ጠንካራ ጎኖች እና የተወሰኑ ደካማ ጎኖች እንዳሉት ተጠቁሟል። የይዘቶቹ አቀራረብ ወደ ውጤት ተኮር አቀራረብ ያመዘኑ ሲሆን የግልፅነት፣ ለደረጃ መጣኝነት፣ የትክክለኛነትና የወጥነት ችግር አይሎ እንደታየባቸውም ተጠቅሷል። በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፍቱ ለተስተዋሉ ችግሮች መፍትሔ ሀሳቦች ቀርበው ጥናቱ ተጠናቋል። ጥናቱ ይዞት በተነሳው ርዕሰ ጉዳይና የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም በትኩረት ክልሎች፣ አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት በሚሰጥበት ደረጃው (ለአፍ ፈቶች በተዘጋጀው ላይ መጠናቱ)፣ በክፍል

ደረጃ ምርጫ (ከ5-8ኛ) ሁሉንም ክፍል ደረጃዎች በማካተቱ እንዲሁም መጻሕፍቱ ስራ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ መጠናቱ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያያል፡፡

ሌላው ሐዋዝ(2000) "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በአማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንፅፅራዊ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የተጠቀሱት ሁለት ክልሎች በሚጠቀሙባቸው የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በማነፃፀር ተመሳስሎና ልዩነታቸውን ነቅሶ ማውጣት ነው፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና ሰነድ ምርመራ የተጠቀመ ሲሆን በውጤቱም ክልሎቹ መሰረት ያደረጉት አንድ አይነት መርሃ ትምህርት ቢሆንም በአቀራረብና በአደረጃጀታቸው መለያየታቸውን፤ በሁለቱም ክልሎች የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርሆዎችን አልሞ አለመተግበር፤ የፅንሰ ሀሳብ፣ የአርትኦትና ከመርሃ ትምህርት የመውጣት ችግሮች በጥናቱ ሂደት የተደረሰባቸው ግኝቶች መሆናቸውን ጠቅሶ ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጦ ጥናቱን ደምድሟል፡፡ ጥናቱ ይዞት በተነሳው ርዕስ ጉዳይና የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም በትኩረት ክልሎች፣ አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት በሚሰጥበት ደረጃው (ለአፍ ፈቶች በተዘጋጀው ላይ መጠናቱ)፣ በክፍል ደረጃ ምርጫ ሁሉንም ክፍል ደረጃዎች በማካተቱ እንዲሁም መጻሕፍቱ ስራ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ መጠናቱ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያያል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች መካከል የሰሚራ፣ የባዬ፣ ፈለቀችና የተስፋዬ ስራዎች በርዕሰ ጉዳያቸው፣ በናሙናነት የተመረጡ መጽሐፍት ማለትም በየክልል ትምህርት ቢሮ ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የተዘጋጁ መጽሐፍትን በመጠቀማቸው ቢመሳሰሉም፣ በአጠናን ዘዴያቸው፣ በክፍል ደረጃ ምርጫቸውና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አጠቃቀማቸው ይለያያሉ፡፡ የተስፋዬና ሰሚራ ለ8ኛ ክፍል ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በተዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍት ላይ ሲያተኩር፤ የባዬ እና ፈለቀች ደግሞ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ባሉ መጽሐፍት ላይ ያተኩራል፡፡ በሌላ በኩል ሰሚራ ሰነድ ምርመራ ብቻ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ሲጠቀም የባዬ ከሰነድ ምርመራ በተጨማሪ ጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅን እንደ አማራጭ ተጠቅሟል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት ሰነድ ምርመራን በመጠቀሙ፤ በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ላይ በማተኮሩ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱ ጥናቶች የተጠኑት ተተካሪ መማሪያ መጽሐፍት ለረጅም ጊዜ ካገለገሉ በኋላ

ወይም እያገለገሉ ባሉበት ጊዜ የተጠናባቸው ሲሆን ይህ ጥናት በቅርቡ ስራ ላይ በዋለው ላይ በማተኮሩ፤ ወዘተ በእነዚህና በመሰል ጉዳዮች የተለየ ነው፡፡

እስከ አሁን ያየናቸው ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ የቀረቡ ጥናቶች ሲሆን ጥናቶቹ እርስ በርሳቸው የሚያመሳስላቸውና የሚያለያያቸው ጉዳዮች እንዳላቸው ሁሉ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ጉዳዮች ቢኖሩም በሁሉም ነገር ግን አንድ አይነት ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ጥናቶቹ አንግበው ከተነሱት የጥናቱ ዓላማ፣ ከመማሪያ መጽሐፍት የክፍል ደረጃ ምርጫና አዘጋጅ ክልል፣ ታትመው አገልግሎት ላይ የዋሉበት ዘመን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አጠቃቀም፣ መጻፎቹ የተዘጋጁበት፣ ተማሪ ምርጫ እንዲሁም የአጠናን ዘዴ፣ ወዘተ አንጻር ልዩነት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም ሲሆን ጥናቱ ይህንን ዓላማ ለማሳካት እንደ ዋና የመረጃ ምንጭ አድርጎ የተጠቀመው ለኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች የተዘጋጀውን 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን ተጠቅሟል።

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የጥናቱ ዓላማ ለኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም ሲሆን የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አገልግሎት ላይ ውለዋል። ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በጽሁፍ መልክ የሚዘጋጁ የትኛውንም አይነት የታተሙ ይሁን ያልታተሙ ሰነዶችን አጥኚው በጥናቱ ውስጥ በሚጠቀምበት ጊዜ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑን (ያለው 2009፤ 196-197) ይገልጻል። በዚህ መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ ሰዋስው ይዘቶች ተሰብስበው ትንተና ተደርጎባቸዋል።

## 3.3 ናሙና አወሳሰድ

### 3.3.1 የመማሪያ መጻሕፍት ናሙና አውሳሰድ

የሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2014 ዓ.ም በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በሙከራ ደረጃ ሲሰጥ ቆይቶ በ2015 ዓ.ም በሁሉም ትምህርት ቤቶች እየተሰጠ ይገኛል። በእርከኑ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ እና አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚል የተዘጋጁ ሁለት መጻሕፍት ሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ይህ ጥናት አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚል የተዘጋጀውን 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍትን በአመቺ (ግኝት) ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። ምክንያቱም አጥኚው

በሚገኝበት አከባቢ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚል የተዘጋጁ መማሪያ መጻሕፍት ስለሚገኙ በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል።

የሰባተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻሐፉ መርሃ ትምህርቱን መሠረት አደርጎ በመዘጋጀት የመርሃ ትምህርቱን አብይና ንዑሳን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ቀርቧል። መማሪያ መጻሐፉ አስር ምዕራፎች፣ አንድ መቶ ሃያ ስድስት ገፆች፣ አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት አጠቃላይ መልመጃዎች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት ነጥብ የሆኑ ሃያ አምስት የሰዋስው መልመጃዎች እና ዘጠኝ ገለጻ የተሰጠባቸው የሰዋስው ይዘቶች ናቸው።

እንደ ሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ሁሉ የስምንተኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፉ መርሃ ትምህርቱን መሠረት አደርጎ በመዘጋጀት የመርሃ ትምህርቱን አብይና ንዑሳን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ቀርቧል። መማሪያ መጻሐፉ ባጠቃላይ አንድ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ የተለያዩ መልመጃዎችና ሃያ ሁለት ገለጻዎች ቀርበዋል። ከእነዚህ መካከል አርባ አራት መልመጃዎችና  አስራ ሁለት ገለጻዎች በሰዋስው ትምህርት ይዘት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

በመሆኑም በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተካተቱ በርካታ ትምህርት ይዘቶች ማለትም በአራቱ ቋንቋ ክሂሎች፣ በስነ-ጽሁፍና ስነ-ልሳን እውቀት ላይ የሚያተኩሩ ይዘቶች የተካተቱ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ይህ ጥናት "የስነ-ልሳን ዘርፍ" የሆነውን "ሰዋስው" የሚለውን ንዑስ ርዕስ በክልል (በቡድን) ንሞና (Area or Cluster Sampling) ዘዴ ተመርጧል።

### 3.3.2 የክልልና የክፍል ደረጃ ናሙና አመራጥ

በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን ኢትዮጵያ 12 ክልሎች ይገኛሉ። እንደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ትምህርት ፖሊሲ እነዚህ ክልሎች ደግሞ ለራሳቸው በሚመቻቸው መንገድ የመካከለኛ ደረጃ (የ7ኛ እና 8ኛ) ክፍል የተማሪ እና መምህሩ መምሪያ መጽሐፍት ያዘጋጃሉ። ከእነዚህ 12 ክልሎች መካከል ይህ ጥናት በደቡብ ክልል ላይ ብቻ ተወስኖ በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ላይ አተኩሯል። ተተኳሪ ክልል በአመቺ ናሙና ዘዴ የተመረጠ ሲሆን የክፍል ደረጃው ደግሞ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ተመርጧል። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው በቀረቡ መማሪያ መጻሕፍት ዙሪያ የተጠኑ ስራዎችን ለማግኘት ዳሰሳ ባደረኩበት ወቅት ደቡብ ክልልን ጨምሮ በርካታ ጥናቶች እንዳሉ ለማግኘት ተችሏል። ነገር ግን በ2014 ዓ.ም በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍቱ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ምንም አይነት የተጠና ስራ ባለመገኘቱ ነው።

## 3.4 መረጃ መተንተኛ ዘዴ

በሰነድ ምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገላጭ ስልት ተንትኗል፡፡ ትንታኔውና ግምገማውም በክለሳ ድርሳናት ላይ በቀረቡ ንድፈ ሀሳባዊ ብያኔ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ግምገማ ተደርጎ ይዘቶቹ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ኢ-አፍ ፊት ለሆኑ ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ተደርጓል፡፡ ግምገማው በክለሳ ድርሳን ላይ በተጠቀሰው ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔ እና የጥናቱ አጠናን ዘዴ መሰረት የተደረገ ሲሆን በ2014 ዓ.ም በሙከራ ደረጃ ሲሰጥ ቆይቶ በ2015 ዓ.ም ወደሙሉ ትግበራ በተገባው መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡

## 4.1 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.1.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር

ይህ አቀራረብ ስልት በመጀመሪያ የሚቀርበውን ሰዋስው ትምህርት ይዘት አስመልክቶ የቋንቋዉ ሥርዓት የሚፈቅደውን ወይም የሚከተለውን ህግ መነሻ ያደረገ ማብራሪያና ትንታኔ በምሳሌ አስደግፎ ካቀረበ በኋላ ተማሪዎች ህጉን መነሻ በማድረግ የሚቀርቡላቸውን መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚያስችል አቀራረብ ስልት ነው፡፡

#### 4.1.1.1 በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በመጽሐፉ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግ በምሳሌ የታገዘ ማብራሪያና ገለጻ ከቀረበ በኋላ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ማብራሪያዎች መሰረት በማድረግ ሌሎች የቀረቡላቸውን ሰዋስዋዊ ትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚያደርጉ ይዘቶችን አካቷል፡፡ በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ የታዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በስነ-ድምጽ፣ በስነ-ምዕላድ፣ በስነ-ፍቺ፣ በስነ-አገባብና አያያዥ ቃላት (አጣማሪዎች) ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

**ሰንጠረዥ 1. በሰባተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሰዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ ገለጻ የተሰጠባቸው ርዕሰ ጉዳዮች የሚያመለክት፦**

| ተ.ቁ | አብይ የሰዋስው ይዘቶች | ገለፃ የተሰጠባቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ገፅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስነ-ድምፅ | የድምፅ ጥብቀት | 30 |
| | | ቃላትን በትክክል መጥራት | 63 |
| 2 | ስነ-ምዕላድ | ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር | 24-25 |
| | | የቃል ክፍሎች መለየት | 40 |
| 3 | ስነ-ፍቺ | የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ | 12 |
| 4 | ስነ-አገባብ | ነጠላና ድርብ ዓ.ነገሮችን መመስረት | 26-27 |
| | | ዓ.ነገር ክፍሎችን መለየት (ስማዊና ግሳዊ ሀረግ) | 51-52 |
| | | ሰዋስው | 54 |
| 5. | አጣማሪዎች | አጣማሪዎች (አያያዥ ቃላት) | 49-50 |

ይህ አቀራረብ ከትምህርቱ ይዘት አንጻር ተማሪው የቀረበውን ቋንቋ ስርዓት ቀድሞ በመረዳት ቀጥሎ የሚቀርበዉን ሰዋስው ትምህርት በቀላሉ እንዲተገብሩ ስለሚያስችል እንደ ጠንካራ ጎን ሊታይለት የሚችል ነው፡፡

ለምሳሌ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከስነ-ምዕላድ ጋር ተያይዞ በምሳሌ የታገዘ ማብራሪያ ለተማሪዎች ቀርቦ ስርዓቱን ከለዩ በኋላ የቀረቡትን መልመጃዎች እንዲሰሩና በቋንቋው ስርዓት እየተመሩ ወደተፈላጊው ግብ እንዲደርሱ የቀረበ የሰዋስው ትምህርት ይዘት በ7ኛ ክፍል ገጽ /30/ ከድምፅ ጥብቀት ጋር የተያያዘ እናገኛለን፡፡

*ማስታወሻ*

*የድምጽ ጥብቀት ማለት በቃላት ውስጥ የሚገኙ ድምጾች ጫን ወይም ረገጥ ተደርጎ መጠራት ማለት ነው፡፡ ድምጾች ጠብቀውና ላልተው በመነበባቸው የትርጉም ለውጥ ያመጣሉ ማለት ነው፡፡*

*(7ኛ ገጽ 30)*

ጥብቀት በቋንቋው ፍቺ ስርዓት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ቃላት በተናጠል ጠብቀው ወይም ላልተው መነበባቸውን ማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህንን ተማሪዎች ቀድመው እንዲረዱ ታሳቢ በማድረግ ማብራሪያ ማቅረቡ እንደጠንካራ ጎን የሚታይለት ነው፡፡

ሌላው በስነ-ድምፅ አብይ ሰዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ *"ቃላትን በትክክል መጥራት"* በሚል ገጽ 63 ላይ የቀረበውን ብንመለከት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድምፅ ጣልቃ ገብነት እንደሚያስቸግራቸው የሚጠቁም መረጃ እናገኛለን፡፡ ድምጾቹን በትክክል አለመጥራትና አለመጻፍ በቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት ላይ አሉታዊ ተጽኖ ማሳረፉ አይቀሬ ነው፡፡ ማለትም የቃላቱን ንበትና ትርጉም (የፍቺ ስርዓት) ያዛባል፡፡

ለምሳሌ:- *"በኮንሶኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች "ዘ"ን በ"ሰ" ቀይረው ይጠራሉ፡፡ በዚህ መሠረት "ዘመረ" በማለት ፈንታ "ሰመረ" ብለው ይጠራሉ" (7ኛ ገጽ 63)፡፡*

ችግሩ ሁሉም በሚባል ደረጃ አማርኛ ኢ-አፍ ፈት በሆኑ ተማሪዎች ላይ የሚከሰት ነው፡፡ ችግሩም እንደ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አይነት የተለያዩ እንደሆነም ማወቅ ይቻላል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛ መንስኤው ድምጾቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውስጥ አለመኖራቸው እና አንዳንዴም በአጠራር ተቀራራቢነት ያላቸው ድምጾች አለመኖሩ እንደሆነም መማሪያ መጽሐፉ ያስቀምጣል፡፡ አቀራረቡ ይህን የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ማብራሪያ በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ስርዓት እንዲያውቁ ከተደረገ በኋላ ድምጾቹን ደጋግሞ በመጥራትና በመለማመድ ችግሩን እንዲያስወግዱ በምሳሌዎች አስደግፎ አቅርቧል፡፡

በእርግጥ ችግሩ በዚህ መንገድ በቀላሉ ይወገዳል ለማለት ሙሉ ለሙሉ ላያስደፍር ይችላል፡፡ ተማሪዎች አስቀድመው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ድምጾች ንበትም ሆነ አገባብ ከታላሚው ቋንቋ ድምጾች ጋር ያለውን ልዩነት በደንብ ካለዩ (ካልተረዱ) አስቸጋሪ ነው፡፡ ችግሩ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋ ለሆኑ አማርኛ ቋንቋ መምህራን ዘንድም በስፋት ይስተዋላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረበው ማብራሪያና በምሳሌ የተደገፈው ገለጻ ችግሩን በተወሰነ መንገድ ለመፍታት የተሻለ በመሆኑ እንደጠንካራ ጎን የሚታይ ነው፡፡

ሌላው "*ማስታወሻ"* በሚል አብይ ርዕስ ስር *"ሰዋስው"* በሚል ንዑስ ርዕስ ገጽ 54 ላይ የቀረበውን ስንመለከት በምሳሌ የታገዘ ማብራሪያና ገለጻ ቀርቦ እናገኛለን፡፡ በይዘቱ ዙሪያ ገለጻ እና ማብራሪያ መቅረቡ መልካም የሚባል ነው፡፡ ነገር ግን የቀረበው ማብራሪያ ስለ ሰዋስው በበቂ ሁኔታ ያሳውቃል ማለት አይደለም፡፡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ማስታወሻ*

*ሰዋስው በአረፍተ ነገር መዋቅር ቃላትና ሀረጋት የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቀው በአግባቡ መቀናጀታቸውን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው። ቃላትና ሀረጋት ሥርዓታቸውን ጠብቀው በአግባቡ ካልተዋቀሩ /ካልተቀናጁ በአረፍተ ነገሩ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ሊዛባ ይችላል። የሰዋስው መዛባት ከሚያመጡ ምክንያቶች አንዱ የአረፍተ ነገር ባለቤትና ግሱ በመደብ፣ በፆታና በቁጥር አለመስማማት ነው።*

***ምሳሌ፡-**በመልካም ስራቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ በርካታ ሰዎች በየአካባቢያችን አለ። በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ **"ሰዎች"** የሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነው ቃል ሰዎቹ **በቁጥር ብዙ** መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን **"አለ"** የሚለው ግስ ግን **ነጠላ ቁጥርን** የሚያመለክት ነው። በመሆኑም በባለቤቱና በግሱ መካከል የቁጥር አለመስማማት ችግር አለ ማለት ነው። አረፍተ ነገሩን አስተካክለን ስንጽፈው እንደሚከተለው ይሆናል። በመልካም ስራቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ በርካታ ሰዎች በየአካባቢያችን አሉ። በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትን የገለጽንበት መደብ፣ ፆታና ቁጥር በግሱ ውስጥ ተመሳሳይ ሆኖ መገለጽ አለበት።*

*7ኛ፡ገጽ/54/*

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው ሰዋስው፤ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት እንደሆነ ነው። በዚህ ክፍል ላይ ለሰዋስው የተሰጠው ብያኔ ከአረፍተ ነገር አንጻር ነው ማለት ይቻላል። በተለያዩ ሰዋስው መጽሐፍት ውስጥ የመስኩ ምሁራን እንደ ገለጹት ሰዋስው የማንኛውም ቋንቋ መሠረት ከሆነው ከድምፅ አንስቶ ሰፋፊ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት ድረስ ያለውን የሚመለከት እንደሆነ ያስገነዝባል። ቀደም ስል እንደተገለጸው በዚህ ክፍል ለሰዋስው የተሰጠው ብያኔ ይህንን የዘነጋ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ሰዋስው የቋንቋ መሰረት ከሆነው ከድምፅ ቅንጅት ጀምሮ እስከ ሰፊ የአረፍተ ነገር መዋቅር ድረስ የሚዘልቅ ነው ከተባለ በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለሰዋስው የቀረበው ገለጻ እነዚያን ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ መጥቀስ ነበረበት። ስለቃላት ቅጥያ አቀባበል፣ የሀረጋት አወቃቀር፣ በዓ.ነገር ውስጥ የተሳቢዎች ሚና፣ የትኞቹ ገላጮች ከየትኛው ቃል ጋር መዋቀር እንዳለበት መገለፅ ነበረበት። ስለሆነም በዚህ ክፍል ስለሰዋስው የተሰጠው ብያኔ በዓ.ነገር አወቃቀር ላይ ብቻ የሚያተኩር በሚመስል መገለፁ ጉዳዩ ላይ ውስንነት እንዲታይ አድርጎታል።

ሆኖም በተተኳሪ መጽሐፉ አስቀድሞ በእነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ በሠንጠረዥ-3 ላይ እንደተጠቀሰው በምሳሌ የታገዘ ገለጻና ማብራሪያ ቀርቦ ሌሎችን የሰዋስው ይዘቶች እንዲለዩ መቅረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.1.1.2 በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በመጽሐፉ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግ በምሳሌ አስደግፎ ማብራሪያና ገለጻ ከቀረበ በኋላ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ሌሎች የቀረቡ ሰዋስዋዊ ትምህርት ይዘቶችና መልመጃዎች እንዲረዱና እንዲሰሩ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ታይቷል፡፡ በ8ኛ ክፍል ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠቅለል ባለ ሁኔታ በስነ-ምዕላድና በስነ-አገባብ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሆነው እናገኛለን፡፡ በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

**ሰንጠረዥ** 2. በስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሰዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ ገለጻ የተሰጠባቸው ርዕሰ ጉዳዮች የሚያመለክት፦

| ተ.ቁ | አብይ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶ | ገለጻ የተሰጠባቸው ንዑሳን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | የሚገኙበት ገጽ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስነ-ምዕላድ | የቃላት ቃል ክፍሎች | 39፣40፣41፣ 42፣78-80 |
| | | የስም እርባታ ለቁጥር | 50-51 |
| | | የስም እርባታ ለጾታ | 51-52 |
| | | የስም እርባታ ለሙያ | 52-53 |
| | | ጊዜ | 53-54 |
| 2 | ስነ-አገባብ | ሰዋስው (አሉታዊና አዎንታዊ ዓ.ነገር) | 61-62 |
| | | የዓረፍተ ነገር ክፍሎች | 80-82 |

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው በ8ኛ ክፍል በምሳሌ ታግዞ ማብራሪያና ገለጻ ከቀረበ በኋላ ሌሎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚያደርግ አካሄድን የተከተሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በስነ-ምዕላድና በስነ አገባብ ዙሪያ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ይዘቶች ተማሪዎች ቃላትን በቃል ክፍላቸው ለይተው እንዲመድቡ የሚያዙ፤ ከቃል ክፍሎች ስም ለቁጥር፣ ለጾታና ለሙያ እንደሚረባ፤ ድርጊት የሚፈጸምበት ወይም የተፈጸመበትን ጊዜ የሚያመለክቱ ግሶችን እንዲለዩ ለማስቻል የታለሙ፤ አረፍተ ነገር በስማዊና ግሳዊ ሀረግ እንደሚከፈልና ስማዊ ሀረጉ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ያለበት፣ ግሳዊ ሀረጉ ደግሞ ማሰሪያ አንቀጽ ያለበት ክፍል መሆኑን ወዘተ በምሳሌ አስደግፎ በጽንሰ ሀሳቦቹ ዙሪያ ገለጻና ማብራሪያ ቀርቦ ቀጥሎ ህጉን እንዲተገብሩ የሚያስችል ወይም ስለጽንሰ ሀሳቦቹ ሰዋስዋዊ ህግ የሚነግሩ መመሪያዎች ከቀረበ በኋላ የሚተገበሩ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

በስነ-ምዕላድ አብይ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ ከቃል ክፍል ጋር ተያይዞ ከገጽ /39-43/ በተከታታይ የሚከተለውን እናገኛለን።

*ትምህርት ስድስት፦ የቃል ክፍሎች (ስምና ተውላጠ ስሞች) /ገጽ 39/*
*ትምህርት ሰባት፡- የቃል ክፍሎች (ተውሳከ ግስና ግስ) /ገጽ 40-41/*
*ትምህርት ዘጠኝ፡- ቃላትን በቃል ክፍሎች መመደብ /ገጽ 42-43/*

በዚህ ክፍል አረፍተ ነገር ከቃል ክፍሎች እንደሚመሠረት ያስገነዝበናል። ቃል ክፍሎችም በአረፍተ ነገር ውስጥ የራሳቸው ሙያ እንዳላቸውም ይጠቁማል። በዚህ መሰረት በአረፍተ ነገር ውስጥ ስም ባለቤትና ተሳቢ ሆኖ እንደሚገኝ፤ ተውሳከ ግሶች ከጊዜና ከሁኔታ አንጻር ግስን እንደሚገልጹ፤ ግሶች ደግሞ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ተገኝተው ድርጊትን እንደምገልጹ፤ ሌላው ደግሞ ግስ የመሆንና የድርጊት ግሶች ተብለው እንደሚከፈሉ በተተኳሪ መጽሐፉ አስቀምጧል። ተውላጠ ስሞች ደግሞ ጠቋሚዎች መሆናቸውን ለይቶ ካስቀመጠ በኋላ በቀረበው ገለጻ መሰረት የሚሰሩ መልመጃዎችን አስቀምጧል። እያይዞ ከላይ በተሰጠው ገለጻ መሰረት የሚሰራ የተለያዩ መልመጃ አስፍሯል። ምንም እንኳን በይዘቶቹ ዙሪያ ማብራሪያዎችና ገለጻዎች ብቀርቡም በቂ አይደሉም። ባንዳንድ ጽንሰ ሀሳቦች ዙሪያ የተሰጡ ገለጻዎች ግልጽና ዝርዝር ሆነው አልቀረቡም።

ከተውላጠ ስም ጋር ተያይዞ እዚህ ቦታ ላይ ሁለት ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል። የመጀመሪያው ሁሉንም ተውላጠ ስሞች እንደ ጠቋሚ የተገለጸበት ነው። በተለያዩ የሰዋስው መጽሐፍት ውስጥ ተውላጠ ስሞች የስም ምትክ መሆናቸውንም (ጌታሁን 1990፡ 49-50፤ 2013፡ 58-69፤ ባየ 2002፡ 39-59) ይገልጻሉ። ነገር ግን በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተውላጠ ስሞች ጠቋሚ አድርጎ አስቀምጧቸዋል። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

*1."ተውላጠ ስሞች ጠቋሚዎች ናቸው። የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ።*

*ምሳሌ፦ **እኔ** ተማሪ **ጠንክር** አባላለሁ። ወንድሜ **ዘርጋ** ይባላል። **እሱ** ወታደር ነው። አህቴ ደግሞ **ቆንጂት** ትባላለች። **እሷ** ባለትዳር ነች። እኛ ሁላችንም የኖርነው በመተጋጋዝ ነው።*

- ***እኔ** የሚለው ቃል **ጠንክር** የሚለውን ስም ይጠቁማል።*
- ***እሱ** የሚለው ቃል **ዘርጋ** የሚለውን ቃል ይጠቁማል።*

- *እሷ የሚለው ቃል ቆንጂት የሚለውን ይጠቁማል፡፡*
- *እኛ የሚለው የሚጠቁመው ሶስታችንን ነው፡፡ ገጽ /39/*

*2.ተውላጠ ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውሰጥ ጠቋሚ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ገጽ /42/*

ከላይ የቀረበው መረጃ ተውላጠ ስሞች ጠቋሚ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በሰዋስው መጻሕፍት ላይ እንደተገለጸው ተውላጠ ስሞች ሁሉም ጠቋሚዎች አይደሉም፡፡ "ከተውላጠ ስሞች መካከል እሱ፣ እሷ፣ እና እነሱ የተባሉት እንደ ጠቋሚ መስተዓምር ያገለግላሉ"(ጌታሁን 2013፡ 58)፡፡ ነገር ግን ከምሳሌው ቀጥሎ ባለው መግለጫ ላይ ሁሉንም ተውላጠ ስሞች እንደ ጠቋሚ አድርጎ አቅርቧል፡፡ ሁሉንም ተውላጠ ስሞችን በጅምላ ጠቋሚዎች ናቸው ከማለት ይልቅ ጠቋሚ የሆኑትን ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡

ሁለተኛው ተውላጠ ስምን ራሱን የቻለ እንደ አንድ የቃል ክፍል ያቀረበበት ነው፡፡ በዘመናዊ ሰዋስው መጽሐፍት ውስጥ ተውላጠ ስም ራሱን የቻለ ቃል ክፍል ሳይሆን በስም የቃል ክፍል ውስጥ የሚመደብ መሆኑን (ጌታሁን 1990፡ 49-50፤ 2013፡ 58-69፤ ባየ 2002፡ 39-59) ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ቃላትን በቃል ከፍላቸው መመደብ*

*እስካሁን ባለው ትምህርት ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ ስትጠቀሙ ነበር፡፡ እነዚህ ቃላት ስሞች፣ ተውላጠ ስሞች፣ ተውሳከ ግሶችና ግሶች ናቸው፡፡ ቃላትን ለመመደብ ከሚያስችለን መስፈርት አንዱ አገባብ ሲሆን ሌላው ደግሞ ቅርጽ ነው፡፡ አረፍተ ነገር ስትመሰርቱ አስተውላችኋል?*

1. *ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውስጥ በባለቤትና በተሳቢ ቦታ ይገኛሉ፡፡*
2. *ተውላጠ ስሞች በአረፍተ ነገሮች ውሰጥ ጠቋሚ ሆነው ያገለግላሉ፡፡*
3. *ተውሳከ ግሶች ከግስ ቀድመው በመገኘት ግሱን ይገልጻሉ፡፡*
4. *ግሶች በአረፍተ ነገር መጨረሻ ይገባሉ፡፡*

*8ኛ፦ገጽ /42/*

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች "የስሞችን፣ የተውላጠ ስሞችን፣ የተውሳከ ግሶችንና የግሶችን" ሙያና ተግባር በአረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም የቀረቡ ቃላትን ከቀረበው ገለጻ አንጻር ለይተው እንዲመድቡ ያዛል፡፡ እንግዲህ የቃል ክፍሎችን ለይተው ሲያስቀምጡ "ተውላጠ ስምን" የመደበው በስም ቃል ከፍል ውስጥ ሳይሆን ለብቻው ራሱ የቻለ የቃል ክፍል በሚመስልና በአረፍተ ነገር ውስጥ ተግባሩ "ጠቋሚ መስተዓምር" አድርጎ ነው፡፡

በሌላ በኩል ተውላጠ ስም በስም የቃል ክፍል የሚመደብ ይሁን ሌላ የተገለጸ ነገር አይታይም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በተጠቀሰው ክፍል ላይ ከቃል ክፍሎች መካከል ስም፣ ግስ፣ ተውሳከ ግስና "ተውላጠ ስም" ብቻ እንደሚያነሳና ሌሎቹ (ቅጽልና መስተዋድድ) እንደማይነሱ ፍንጭ አልተሰጠም፡፡ በመሆኑ ጉዳዩ የግልጽነት ችግር እንዳለበት ያሳያል፡፡

### 4.1.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

በዚህ ስልት የሚቀርብ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አስቀድሞ በተመረጡ ሰዋስው ይዘቶች ዙሪያ ምሳሌዎች ይቀርብና በምሳሌዎች እየተመሩ መልመጃዎችን በመስራት በራሳቸው ጥረት የቋንቋውን ስርዓት ለይተው እንዲገነዘቡ የሚያስችል ስልት መሆኑን በክለሳ ድርሳን ክፍል ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

በተተኪ 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በገጽ 12፣ 51 እና 53 ላይ የሚከሉትን እናገኛለን፡፡

*ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡*

| *ቃላት* | *የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ* |
|---|---|
| *ምሳሌ፡- ታማኝነት* | *ቃልን መጠበቅ፣ አለማጭበርበር፣ አለመስረቅ* |

*ገጽ፡- /12/*

ሌላው በገጽ /51/ ላይ "የአረፍተ ነገር ክፍሎችን መለየት" በሚል ዋና ትምህርት ርዕስ ስር ተግባር.1 የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

<u>*በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊ ሀረጉንና ግሳዊ ሀረጉን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡*</u>

*ምሳሌ፡-* <u>*የዘንድሮው ምርጫ*</u> */*<u>*በሰላም ተጠናቀቀ፡፡*</u>

*ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ*

እንዲሁም ገጽ /53/ ላይ <u>*ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች በመመልከት በምሳሌው መሰረት የሰዋስዉ ችግሩ ምን እንደሆነ ግለጹ*</u>

*ምሳሌ፡- ላሚቷ ሳር በላ፡፡ የፆታ አለመስማማት*

ከላይ የምንመለከታቸው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የምናገኛቸው ትዕዛዞችና ምሳሌዎች ናቸው። ለአብነት ሶስተኛውን ምሳሌው ብንመለከት በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተፈጠረው ሰዋስው ስህተት የጾታ አለመጣጣም መሆኑን ነው። በባለቤቱ ቦታ ላይ የምናገኘዉ "ላሚቷ" የሚለው ቃል እንስት (ሴት) ጾታን የሚያመለክት ነው። ማሰሪያ አንቀጹ ላይ የሚገኘዉ ደግሞ ተባት ማለትም /በል-ኣ/ "በል" በሚለው ግስ አምድ ላይ የሚናገኘው /-ኣ/ ተባት ጾታ አመልካች በመሆኑ በአረፍተ ነገሩ ዉስጥ የጾታ አለመስማማት መከሰቱን በምሳሌ አስቀምጧል። በዚህ መሰረት ተማሪዎች ቀድሞ በቀረበው ምሳሌ እየታገዙ ሌሎች መልመጃዎችን እንዲሰሩ የሚጋብዝ አቀራረብ በመሆኑ ይዘቱ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበ ነው።

በ8ኛ ክፍል *መማሪያ መጽሐፍት* /ገፅ 16/ *በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡትን የህይወት መመሪያዎችን እናንተ እንደተናገራችኋቸው አድርጋችሁ ጻፏቸው።*

*ምሳሌ፡- ሀ. ሰዎች እንዲያከብሩኝ እኔም አከብራቸዋለሁ።*

ከዚህ የምንረዳው አስቀድሞ ለተማሪዎች "የህይወት *መመሪያ*" በሚል ርዕስ በሶስተኛ ወገን የተተረከ ሀሳብ እንዳለ ነው። ትዕዛዙ ላይ እንደተገለጸው ይህንን በሶስተኛ ወገን የተተረከውን ሀሳብ ተማሪዎች ራሳቸው እንደተናገሩቿኋቸው በማድረግ ሀሳቦቹን በ1ኛ መደብ እንዲጽፏቸው የሚያደርግ ነው። ሂደቱ ተማሪዎች በምሳሌዎች እየታገዙ ከዝርዝር ሰዋስው ወደ አጠቃላይ ሰዋስው ህግ እየተመሩ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያደርግ መሆኑን መረዳት ይቻል።

ሌላው በተተኳሪ 8ኛ ክፍል /ገጽ 29/ ላይ "የቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች" በሚል ርዕስ ስር

*ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ስርዓተ ፆታ በሚል ርዕስ ስር ካዳመጣችሁት ምንባብ የወጡት ናቸው። በምሳሌው መሰረት ለቃላቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ መዝገበ ቃላዊ ፍች ስጡ።* ከትዕዛዙ ቀጥሎ በሰንጠዥ ውስጥ ለአንድ ቃል ምሳሌ ከተሰጠ በኋላ ተማሪዎች ሌሎቹን እንዲሰሩ ቃላትን ዘርዝሯቸዋል። እነዚህ አስቀድመው ለተማሪዎች በቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ዙሪያ ምሳሌዎችን በመስራት በተሰራዉ ምሳሌ ተንተርሰዉ በራሳቸዉ ወደ ተፈላጊው ሰዋስው ህግ ላይ እንዲደርሱ የሚያደርጉ በመሆናቸዉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ ናቸው ማለት ይቻላል።

### 4.1.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ

በክለሳ ድርሳን ክፍል እንደተጠቀሰው ይህ የአቀራረብ ስልት በታላሚ ቋንቋ ቅርጽ ዙሪያ ባለው ህግጋት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት በተተኳሪዎቹ መጽሐፍት ውስጥ ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረቡ ይዘቶችን እንደሚከተለው እንመልከት፡-

#### 4.1.3.1 በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በርከት ያሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በውጤት ተኮር አቀራረብ ስልት ቀርበዋል፡፡ በገጽ 24፣ 25፣ 26፣ 27 (ተግባር.1)፣ 41 (ተግባር.1)፣ 42 (ተግባር.2)፣ 51 (ተግባር.1)፣ 53 እና 56 ላይ የሚገኙት ይጠቀሳሉ፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፦

*"ትምህርት አምስት፡- ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል"* በሚል ትምህርት ርዕስ ስር ሁለት ይዘቶች በውጤት ተኮር ስልት ቀርበዋል፡፡

*የመጀመሪያው፡- ቀጥሎ የቀረቡትን ምዕላዶች ነጥላችሁ አስቀምጡ*

*1. ቤቶች 2. ወንድሜ 3. ደብተሩ (ገጽ 24)* የሚል እናገኛለን፡፡

ከላይ ከቀረበው መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ቀላቱን በምዕላድ ከፋፍለው እንዲያስቀምጡ የሚሳይ ነው፡፡ ይህ ማለት ቃላት በምዕላድ ሲከፋፈሉ የራሳቸው የሆነ ቅርጽ ማለትም "ነፃ" እና "ጥገኛ" የሚል አላቸው፡፡ መልመጃው ተማሪዎች ይህንን ቅርጽ ለይተው እንዲያስቀምጡ የቀረበና በቅርጽ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የቀረበውን መልመጃ ትዕዛዝ ስንመለከት አሻሚ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በትዕዛዙ ላይ እንደምንመለከተው ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ምዕላዶች ነጥለው እንዲያስቀምጡ ያዛል፡፡ ከታች ደግሞ የተሰጡት ደግሞ ከምዕላድ የሰፋ መዋቅር ነው፡፡ በተለያዩ የሰዋስው መጻሕፍት ውስጥ ምዕላድ ልነጠል የማይችል የመጨረሻ ንዑስ አሀድ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ልነጣጠል የሚችለው ምዕላድ ሳይሆን ቃል ነው፡፡ ነገር ግን ምዕላድን የሚነጠል አድርጎ ማምጣቱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንደ ደካማ ጎን ልጠቀስ ይችላል፡፡

*ሁለተኛው ደግሞ ቀጥሎ የተሰጡትን ምዕላዶች በማቀናጀት ቃላትን መስርቱ /ገጽ 25-26/፡፡*

ከዚህ መረጃዎች የምንገነዘበው ተማሪዎች ተነጥለው የተቀመጡ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን በማጣመር ቃላትን እንዲመሰርቱ የሚያዝ ነው፡፡ ተማሪዎች ስለምዕላድ የተረዱትን በተግባር እንዲያሳዩ የሚያደርግ በመሆኑ በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረበ ነው፡፡

በስነ-አገባብ ትምህርት ዙሪያ ገጽ /27/ ተግባር 1 ስር *አረፍተ ነገሮችን ነጠላና ድርብ* በማለት እንዲለዩ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ሌላኛው ተጠቃሽ ነው፡፡

ትምህርት ሰባት ‹‹ሰዋስው›› በሚል ርዕስ *የቃል ክፍሎች መለየት* በሚል በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረበ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

*በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ስም፣ ቅጽል እና ግስ የሆኑት ቃላትን በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አስቀምጡ_(ገጽ 41 ተግባር 1)፡፡* እንዲሁም

*በየግላችሁ አምስት አረፍተ ነገሮችን መስርታችሁ፤ በመሰረታችሁት አረፍተ ነገር ውስጥ ስም፣ ቅጽል እና ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ /ገጽ 42 ተግባር 2/*

እነዚህ ከላይ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪዎች አረፍተ ነገርን የመሰረቱ ቃላትን በቃል ክፍላቸው ለይተው እንዲመድቡ ለማገዝና ከራሳቸው ቃል ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ለማስቻል የቀረቡ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው በአረፍተ ነገር ውስጥ ቃላት የራሳቸው የሆነ ሙያ አላቸው፡፡ ስለዚህ በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃላትን ሙያ ለይተው በተገቢ ቦታ መጠቀም ለአረፍተ ነገሩ ሰዋስዋዊነት ወሳኝ ነው፡፡ ከላይ ከቀረበው መልመጃ ሁለት ነገሮችን መረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ቃላቱን ከራሳቸው ተጠቅመው አረፍተ ነገር ሲመሰርቱ የተጠቀሙበትን ቃል፣ የቃል ክፍሉን የሚለዩበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሙባቸው ቃላት ሙያ ለይተው በተገቢ ቦታ መጠቀማቸውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተማሩትን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በተግባር የሚያሳዩበት በመሆኑ መልመጃውም ውጤት ተኮር በሆነ መልኩ የቀረበ ነው፡፡

ሌላው ስነ-አገባብን ለማስተማር ከአረፍተ ነገር ጋር የተያያዘ የቀረበውን የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

*አንድ የስም ገላጭና አንድ የግስ ገላጭ ያላቸውን አምስት አረፍተ ነገሮች መስርታችሁ ስማዊ ሀረጉንና ግሳዊ ሀረጉን ለይታችሁ አመልክቱ (ገጽ 51 ተግባር 1)*

ይህ የሰዋስው ትምህርት ይዘት በታላሚ ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ በቅርጽ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ተማሪዎች አረፍተ ነገሮችን ሲመሰርቱ በስማዊ ሀረጉ ክፍል ቅጽልን፤ በግሳዊ ሀረጉ ክፍል ደግሞ ተዉሳከ ግስን የያዘ አረፍተ ነገር ከመሰረቱ በኋላ ስማዊና ግሳዊ ሀረጉን ለይተው እንዲያመለክቱ የሚያዝ በመሆኑ በዉጤት ተኮር የቀረበ ነዉ፡፡

#### 4.1.3.2 በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ

በዚህ ክፍል ደረጃ በገጽ 8፣ 11፣ 30፣ 38-39 (ተግብር 1 እና 2)፣ 43፣ 51 (ተግባር ሀ እና ለ)፣ 52፣ 53፣ 54፣ 62፣ 63፣ 80፣ 81፣ 82 (ተግባር ሀ፣ ለ፣ ና ሐ) ላይ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውጤት ተኮር አቀራረብ ስልት ተከትለው የቀረቡ ናቸዉ።

> *የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ቀድሞ ከቀረበው ጽሑፍ የተወሰዱ ናቸው። ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ለይታችሁ ጻፉ። ገጽ /8/*

ከላይ የቀረበው ትዕዛዝ በመማሪያ መጽሐፉ ገጽ /6/ "የስራ ክፍፍል" በሚል ርዕስ የአንቀጽ አወቃቀር ለማስተማር ከቀረበው ምንባብ የተወሰደ ነው። ምንም እንኳን አንቀጽ ለማስተማር ይቅረብ እንጂ ከሰዋስው መዋቅር አረፍተ ነገርን ደርሶ ነክቶ ያለፈ ነው። አንቀጽ አረፍተ ነገሮች በስርዓት ተቀናጅተው የሚያስገኙት መዋቅር ነው። አንድ አንቀጽ ስዋቀር መታየት ያለበት የአንቀጹ አወቃቀር ብቻ ሳይሆን ዓረፍተ ነገሮቹ በስርዓት መደራጀቱም ጭምር መፈተሸና ማወቅ ተገቢ ነው። አረፍተ ነገሮቹን የሚንፈትሸው ደግሞ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ከማሰሪያ አንቀጽ ጋር ስሚሙ ስለመሆኑ፣ ተሳቢው በተገቢ ሁኔታ ስለመገለጹ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል። መልመጃው የአረፍተ ነገሮችን አወቃቀር ማለትም የአረፍተ ነገሩን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ለይተው እንዲያስቀምጡ ያዛል። በመሆኑም የዚህ ሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ በቀረበው ማሳያ መሠረት ውጤቱን እየለዩ እንዲሄዱ ለማስቻል የቀረበ በመሆኑ ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው በገጽ /30/ *"ትምህርት አስራ አንድ፦ ምዕላዶችን መነጠልና ማጣመር"* በሚል ርዕስ ስር ሁለት ጉዳዮች እናገኛለን። የመጀመሪያው *ቃላትን በምዕላድ መነጣጠል* በሚል እንደሚከተለው ቀርቧል።

> *ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ኤርጎጎና ላጺሶ ከሚለው ምንባብ የተወሰዱ ናቸው። በቀረበው ምሳሌ መሰረት ምዕላዶችን በመነጠል ፃፉ ገጽ /30/።*
>
> ***ምሳሌ፦*** *ሀ/ ቤቶች = ቤት - ኦች*
>
> *ለ/ ልጅነት = ልጅ - ነት*

ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች ቃላትን በነጻና በጥገኛ ምዕላድ ከፍለው እንዲያስቀምጡ ለማስቻል የቀረበ ነው፡፡ በእርግጥ ነጻና ጥገኛ ምዕላድ ምን እንደሆነ ገለጻ ባያስቀምጥም ተማሪው ከቀረበው ምሳሌ ተነስቶ ሁለቱንም እንዲለይ የሚያደርግ አቀራረብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ "ምዕላዶችን ማጣመር" የሚል ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ከዚህ በታች የሰው ልጆች አቅም ከሚለው ምንባብ የወጡ ቃላት በምዕላድ መልክ ቀርበዋል፡፡ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት ምዕላዶችን አጣምራችሁ ጻፉ፡፡*

*ምሳሌ፡- ሀ/ ክብር -ኧት = ክብረት*

*ለ/ ሰልፍ - ኧኛ = ሰልፈኛ*

1. እውነት - ኧኛ = ………………………………….
2. ከ- አንድ -ኧኛ -ው =……………………………
3. የ- ሊቅ -ኣውንት -ኡ = ………………………..
4. ባሪያ -ነት -ኣቸው =…………………………….
5. ፈቃድ -ኣቸው -ን =…………………………….
6. በ- ዕድገት -ኡ = ……………………………….
7. በ- ፈጠረ -ብ -ኣቸው = ……………………….. */ገጽ 30-31/*

መልመጃው ምዕላዶችን አጣምረው ቃል እንዲመሰርቱ የሚያደርግ ነው፡፡ በምሳሌው እንደምንመለከተው የመጀመሪያው /ክብር/ በሚለው ስም ላይ /-ኧት/ የሚል ቅፅል መስራች ቅጥያ ተቀጥሎበት /ክብረት/ የሚል ቅጽል አስገኝቷል፡፡ ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ /ሰልፍ/ በሚለው ስም ላይ ውልድ ቅፅል መስራች /-ኧኛ/ ተቀጥሎበት /ሰልፈኛ/ የሚል ውልድ ቅፅል አስገኝቷል፡፡ በመሆኑም መልመጃው ተማሪዎች በቀረቡ ምሳሌዎች መሠረት ከታች በምዕላድ ተበታትነው የቀረቡትን አቀናጅተው ቃል እንዲመሰርቱ የሚያደርግ ነው፡፡
ምዕላድ ነፃና ጥገኛ ተብለው በሁለት ይከፈላል፡፡ ነፃ ምዕላድ ራሱን ችሎ የሚቆም፣ ብቻውን ትርጉም ያለው አሀድ እንደሆነ እና ጥገኛ ምዕላድ ደግሞ ብቻውን ትርጉም የሌለው፤ ነገር ግን ሰዋስዋዊ ተግባር ያለው መሆኑን ጌታሁን (1989: 43-45) ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ ይህ ብያኔ ቃላትን በምዕላድ ስንከፍል ትኩረት ማድረግ እንዳለብን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ በዚህ ክፍል ለማንሳት የፈለኩበት ጉዳይ ከላይ በቀረበው መልመጃ ስር በተራ ቁጥር "3" እና "7" ስር የተቀመጡት ለምዕላድ ከተሰጠው ብያኔ አንጻር ጥያቄ የሚያጭሩ ናቸው፡፡ በተራ ቁጥር ሶስት ላይ *"የሊቃውንቱ"* የሚለውን ቃል */የ-ሊቅ-ኣውንት-ኡ/* በሚል እና በተራ ቁጥር

ሰባት ስር ደግሞ *"የፈጠረባቸው"* የሚለውን ቃል */የ-ፈጠረ-ብ-ኣቸው/* በሚል በምዕላድ ተተንተኗል። በመጀመሪያው ውስጥ /ሊቅ/በሚለው ነጻ ምዕላድ ላይ የተቀጠለው /-ኣውንት/ የሚለው የእርባታ ይሁን የምስረታ ቅጥያ ምዕላድ የሚታወቅ ጉዳይ የለም። በግዕዙ አበዛዝ ሊቃውንት፣ የሊቅ ብዙ ቁጥር ቢሆንም /-ኣውንት/ በሚል የተቀጠለው ጥገኛ ምዕላድ ከዚህ ቀደም ከሚታወቁ የእርባታና ምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች የተለየ በመሆኑ ተግባሩና ቃሉ በምዕላድ የተከፋፈለበት መንገድ አሻሚ ሆኖ እናገኛለን። በተራ ቁጥር ሰባት /የ-ፈጠረ-ብ-ኣቸው/ በሚለው ውስጥ /-ብ/ በተመሳሳይ ሰዋስዋዊ ተግባሩ ምን እንደሆነ አይታወቅም። በመሆኑ የግልጽነት ችግር አሉባቸው ማለት ይቻላል።

*ቃላትን በቃል ክፍላቸው መደቡ* በሚል ርዕስ ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረበ የሚከተለውን እናገኛለን።

> *ከዚህ በታች በተመለከተው ጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ አረፍተ ነገሮች አሉ። በእነሱ ውስጥ ያሉ ቃላትን በመለየት በሰንጠረዡ ምሳሌ መሰረት በቃል ክፍላቸው መደቡ /ገጽ 43/*

ከዚህ ትዕዛዝ የምንገነዘበው አንቀጽን ያዋቀሩ ቃላት በቃል ክፍላቸው እንዲመድቡ የሚያስችል ነው። እያንዳንዱ ቃል የሚመደብበት የራሱ የሆነ የቃል ክፍል ምድብ አለው። ቃላትን ወስደን በቃል ክፍል ለመመደብ የሚያስችል የየራሱ መመዘኛዎችም ይኖሩታል። ስለሆነም ከላይ የቀረበው መልመጃ ተማሪዎች በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ከዚህ ቀደም ያካበቱትን እውቀት በተግባር እንዲያውሉ የሚያስችል በመሆኑ በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው በቃል እርባታ ላይ ያተኮረ ገጽ /53/ ላይ *"ድርጊት የተፈጸመበት ጊዜን" የሚያሳዩ ቃላት* የሚልና ገጽ /54/ ደግሞ *"ጾታ አመልካች ቅጥያ ያላቸው ቃላት"* በሚል ርዕስ በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረቡትን እናገኛለን።

የመጀመሪያው ጊዜን ለመጠቆም ግስ ላይ ከሚጨመሩ ቅጥያዎች ጋር የተያያዘ ነው። ጊዜ በሶስት ይከፈላል። እነዚህም አሁን፣ ሀላፊና ወደፊት በመባል ይታወቃሉ። ግሶች እነዚህን ለመግለጽ ቅጥያዎችን በመቀበል ይረባሉ። ተማሪዎች ቅጥያዎቹን በግሶች ላይ እየጨመሩ አርብተው እንዲያሳዩ የሚጠይቅ በመሆኑ በውጤት ተኮር አቀራረብ ስልት ቀርቧል። በተመሳሳይ በገጽ /54/ ላይ ጾታ አመልካች ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ከራሳቸው እንዲጽፉ የሚያደርገው ሌላኛው በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረበ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ነው። *ትምህርት ሰባት፡- "የቃላት ምስረታ"* በሚል ርዕስ ስር የሚከተለውን እናገኛለን።

*ከዚህ በታች የቀረቡትን ምሳሌዎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ላይ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጨመር ሌሎች ቃላትን መስርቱ /በገጽ 61/፡፡*

በተመሳሳይ ከላይ ከቀረበዉ ይዘት ጋር በሚመሳሰል *የቃላት ምስረታ* በሚል ርዕስ በውጤት ተኮር ዘዴ የቀረበ የሰዋስው ትምህርት እናገኛለን፡፡

*የሚከተሉትን ስሞች ቅጥያ ምዕላድችን በመጨመር ቅጽሎችን መስርቱ /ገጽ 63/*
*ከዚህ በታች የተሰጡኣችሁን ቃላት የቃል ክፍል ለይታችሁ ጻፉ /ገጽ 80/*

በገጽ /81/ ደግሞ *"አረፍተ ነገርን በስማዊና በግሳዊ ሀረግ ለዩ"* የሚለው፣ እንዲሁም *አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በቃል ክፍላቸው መድቡ (*ገጽ 82) የሚለው እና *ከአረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎችን ለይታችሁ አመልክቱ* (ገጽ 83) እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ትዕዛዞች በቋንቋው ቅርጻዊ ስርዓት ላይ በማተኮር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡላቸውን ትምህርት ይዘቶችን ከተማሩ በኋላ ዉጤቱን እንዲሳዩ የሚጋብዝ በመሆኑ ይዘቶቹ ውጤት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረቡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

### 4.1.4 ሂደት ተኮር አቀራረብ

ይህ አቀራረብ ስልት የሰዋስው ይዘቶች ለተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብበትን ያመላክታል፡፡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተናጠል ሳይሆኑ በአውድ ውስጥ ታቅፈው ጥቅም ላይ እንዲዉል የሚደረግበት ነው፡፡ በመሆኑም በተተኳሪ ክፍል ደረጃዎች አብዛኛው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሂደት ተኮር ዘዴ ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.4.1 በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

በ7ኛ ክፍል ገጽ /10/ ላይ *ትምህርት አምስት፡- "ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት"* በሚል ርዕስ ስር የሚከተለው ትዕዛዝ ይገኛል፡፡

*ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ ለተሰመረባቸው ቃላት እንደ አገባባቸው ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ /ገጽ 10/*

"*የሰላም ዋጋው ስንት ነው?*" በሚል ርዕስ ሁለት ሀረጋትና አስራ አንድ ቃላት በድምሩ አስራ ሶስት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ቀርቧል፡፡ የአቀራረብ ሁኔታው ተማሪዎቹ ለቃላቱና ሐረጋቱ ተናጠላዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ሳይሆን በአውድ ውስጥ የያዙትን ፍቺ እንዲሰጡ የሚያደርግ ነው፡፡ በእርግጥ ለቃላት ፍቺ በመስጠት ሂደት ውስጥ ከአውድ ውጪ የሚሰጠው ፍቺ በተለይ ኢ-አፍ ፊት ለሆነው ተማሪ በመዝገበ ቃላት ካልታገዘ በስተቀር እጅግ አስቸጋሪ

ነው። የቃላቱ ፍቺ በመዝገበ ቃላት ታግዘው ብሰጡም እንኳን ቃላቱን በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ የመጠቀማቸው ሁኔታም እጅግ አነስተኛ ነው። ምክንያቱም ቃላቱ በተናጠል ከመቅረባቸው የተነሳ ሽምድደው ለመያዝ አስቸጋሪ ስለምሆንባቸው ነው። ነገር ግን ሂደት ተኮር በሆነ መልኩ የሚቀርበው ሰዋስው ትምህርት በአውድ ውስጥ ታቅፎ በመቅረቡ ተማሪዎች የቃላቱን ፍቺ በቀላሉ እንዲገምቱና እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። ስለሆነም ከላይ በቀረበው መልመጃ ቃላቱና ሐረጋቱ በአውድ (በምንባብ) ውስጥ መቅረቡ ተማሪዎች የቃላቱንና ሐረጋቱን ፍቺ በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ በቀላሉ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል። በመሆኑ ይዘቱ በሂደት ተኮር የቀረበ ነው።

ሌላው "*ጅምር ሀሳቦችን አሟልቶ መጻፍ*" በሚል ትምህርት ርዕስ ስር የሚከተለውን እናገኛል።

*ከዚህ በታች የቀረቡትን በጅምር የቀሩ ሀሳቦች ከራሳችሁ አሟልታችሁ ጻፏቸው /ገጽ 13/*

ከላይ ከቀረበው መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች የቀረበውን ሀሳብ አሟልተው ይጽፉ ዘንድ መነሻ የሚሆን ሀሳብ ቀርቧል። አቀራረቡ ተማሪዎች የቀረበውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ የራሳቸውን ሀሳብ በሁኔታዎች ሳይገደቡ እንዲጽፉ ያስችላቸዋል። በመነሻ ሀሳቡ መሪነት የሀሳብ ፍሰቱን፣ ሰዋሰዋዊነቱንና ተያያዥነቱን ጠብቀው ሂደታዊ በሆነ መልኩ እንዲፅፉ የሚያደርግ በመሆኑ ሂደት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው የሰዋስው ይዘቶችን በተናጠል ሳይሆን ይዘቶቹ በሚኖሯቸው ትርጉም ለማህበራዊ መስተጋብር አገልግሎት እንዲያውሉ የቀረበ የሚከተለውን እናገኛለን።

*ቀጥሎ መምህሩ የሚያነቡላችሁ ጽሑፍ በየመሀሉ የተጓደሉ ሀሳቦች ያለበት ነው። መምህራችሁ ጽሑፉን ሲያነቡላችሁ የተጓደለውን ሀሳብ በጽሑፍ አሟሉ /ገጽ 16/*

መልመጃው ማዳመጥን ለማስተማር "ዳንቾ ስጋት" በሚል ርዕስ ከቀረበ ምንባብ የተወሰደ ነው። ምንባቡ አንዲት በገጠረ አከባቢ የምትኖር መምህርትና የጤና ባለሙያ የነበረች ሴት በኮቭድ 19 ዙሪያ ስለበሽታው ምንነት፣ መተላለፊያ መንገድ፣ ስለምልክቶቹ፣ ስለመከላከያ መንገድ፣ ስለመተላለፊያ መንገድ፣ ወዘተ ጉዳዮች አንስተው ያደረጉትን ምልልስ የያዘ ነው። ምንም እንኳን ምንባቡ ማዳመጥን ለማስተማር ይቅረብ እንጂ በውስጡ ቃላትን፣ የሀሳብ ቅንጅት (ሰዋስዋዊነት) ለማስተማርም የታሰበ መሆኑን ከትዕዛዙ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ይዘቱ ተማሪዎች ስለኮሮና በሽታ ከዚህ ቀደም የሚያውቁትን ወይም የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው በምንባቡ ውስጥ የተጓደለውን ክፍል እንዲያሟሉ የሚያዝ ነው። ተማሪዎቹ

የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በምንባቡ አውድ እየታገዙ የተጓደለውን ክፍል እንዲያሟሉ የሚስችል በመሆኑ ሂደት ተኮር አቀራረብ ስልት የተከተለ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በገጽ /24/ *ትምህርት አራት፡- "ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት"* በሚል ከምንባቡ ለተወሰዱ ቃላት በምንባቡ ታግዘው ፍቺ እንዲሰጡ የቀረበ ሌላኛው ተጠቃሽ ይዘት ነው፡፡

ከገጽ /35-37/ *ትምህርት አምስት፡- "ግጥምን አንብቦ ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት"* በሚል ርዕስ ስር ሂደት ተኮር በሆነ መንገድ የቀረበ እናገኛለን፡፡ ምንባቡ ተማሪዎች የቃላት እውቀት እንዲኖራቸው ከማስቻል በተጨማሪ ትርጉማቸውን ከአውዳቸው ለመረዳት የሚያስችል ሂደትን የተከተለ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ግጥሙን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ቃላት በተመሳሳይ ፍቻቸው አዛምዱ /ገጽ 36/*

*ግጥሙን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ቃላት በተቃራኒ ፍቻቸው አዛምዱ /ገጽ 37/*

እነዚህ ሁለቱ ትዕዛዞች "*ሀገሬ*" በሚል ርዕስ በቀረበው ግጥም ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ለቃላቱ ፍቺ የሚፈልጉት በተናጠል ሳይሆን በስንኙ አውድ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አንድ ቃል በተናጠል ስታይ በርካታ ፍችዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ ነገር ግን በዓረፍተ ነገር ወይም በስንኝ ውስጥ የሚኖረው ፍቺ አንድ ወይም የተወሰነ ይሆናል፡፡ ከዚህ ሌላ የቃሉ የማያወላውል /ትክክለኛ/ ፍችም በአዉዱ ውስጥ ያለው ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ትኩረት መሰጠት ያለብን ጉዳይ አለ፡፡ ይህም ተማሪዎች ከአውድ ውጪ ለቃላቱ የሰጡትን ፍቺ ከትምህርቱ በኋላ የሚጠቀሙበት ሁኔታ ነው፡፡ ምናልባት ለቃላቱ ፍቺ የሚሰጡት በመዝገበ ቃላት በመታገዝ፣ ሰዎችን በመጠየቅ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ ለቃላቱ ለሰጡት ፍች ያላቸው እውቀት፤ ቃላቱ በዛ ብለው በቀረቡ ቁጥር ፍችያቸውን ሸምድደው ለማህበራዊ መስተጋብር የሚያውሉበት መንገድ፣ እንዲሁም የቃላቱ ፍች ብዛትና ውስብስብነት ለይተው በአውድ ውስጥ መጠቀም አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ከዚህ ይልቅ በአውድ የሚቀርብ የቃላት ትምህርት ለቃላቱ ፍች መስጠት ብቻ ሳይሆን የቃላቱን ፍች በተለያዩ ማህበራዊ አውድ ውስጥ ለመጠቀም ምቹ በመሆኑ በሂደት ተኮር ዘዴ መቅረቡ እንደጠንካራ ጎን ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ሌላው ከቃል ትምህርት ጋር ተያይዞ *ትምህርት ሶስት፡- "ቃላንትን ለመረዳት ማንበብ"* በሚል ርዕስ ስር አንድ ምንባብ ቀርቦ በንባብ ጊዜ ጥያቄነት የቀረበ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

*ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ እያነበባችሁ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በአገባባቸው መሰረት ፍቺ ስጡ /ገጽ 46-48/*

ምንባቡ ተማሪዎችን የንባብ ክሂል ለማስተማር ትኩረት አድርጎ የተዋቀረ ቢሆንም በውስጡ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ይዞ በመቅረቡ እዚህ ቦታ ላይ ሊጠቀስ ችሏል፡፡ ምንባቡ "ስርዓተ ጾታ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ስድስት አንቀጾች አሉት፡፡ በአንቀጾቹ ውስጥ አስራ ሶስት ቃላትና ሰባት ሀረጋት በድምሩ ሃያ (20) አገባባዊ ፍቺ የሚሰጥባቸው የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎች በምንባቡ አውድ ለቃላትና ለሐረጋት እያነበቡ በሂደት ፍቺ የሚፈልጉበት ሂደትን የተከተለ አቀራረብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለቃላቱና ሐረጋቱ ተናጠላዊ ፍቺ እንዲፈልጉ የሚያዝ ሳይሆን በአውድ ታግዘው ፍቺ እንዲሰጡ ማድረጉ ፍችዎቹን በቀላሉ ተረድተው ለተለያዩ አገልግሎት እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

*"አጣማሪዎችን (አያያዦችን) በአረፍተ ነገር ውስጥ መጠቀም"* በሚል ርዕስ ስር ሂደት ተኮር በሆነ መንገድ የቀረበ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

*ቀጥል በሰንጠረዡ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች ከተሰጡት አጣማሪዎች (አያያዦች) መካከል ተገቢውን በመጠቀም የተሟላ ሀሳብ መስርቱ /ገጽ 49/*

| *አረፍተ ነገር* | | *አጣማሪ* | *አረፍተ ነገር* |
|---|---|---|---|
| *1.* | *የሥርዓተ ፆታ አመለካከት ተፈጥሮአዊ አይደለም፡፡* | *ይሁን እንጂ* | *በማህበረሰቡ ሴት ወይም ወንድ በመሆን የሚሰጥ ነው፡፡* |
| *2* | *የማህበረሰባችን አመለካከት ለወንዶች ያደላ ነው፡፡* | *ይልቁንም* | *ለሴቶች የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡* |
| *3* | *ሴቶች በወላጆቻቸው ከፍተኛ ስራ ጫና ይደረግባቸዋል፡፡* | *ስለዚህ* | *ጫናውን ተቋቁመው ለውጤት የሚበቁ ሴቶች አሉ፡፡* |
| *4* | *ከፆታ እኩልነት ጋር የተያያዘ የአመለካከት መዛባት አለ፡፡* | *ነገር ግን* | *ለሴቶች የሚሰጠውን ግምት ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡* |
| *5* | *ሴቶች የማህበረሰቡ ግማሽ አካል ናቸው፡፡* | *በመሆኑም* | *በሚፈለገው መጠን ትኩረት አልተሰጣቸውም፡፡* |

ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች የቀረቡ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን አያያዥ ቃላት በመጠቀም የቋንቋው ሰዋስው አወቃቀር ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት ውስብስብ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያዝ ነው። መልመጃውም አሻሚነት አለው። ከላይ በሰንጠረዡ ግራና ቀኝ አረፍተ ነገሮች ይገኛሉ። በመካከላቸው ደግሞ አጣማሪዎችን እናገኛለን። አረፍተ ነገሮቹና አጣማሪዎቹ እኩል ወደ ጎን እየተሰመሩ ቀርበዋል። ትዕዛዙ ደግሞ ከተሰጡ አማራጭ አጣማሪዎች ተጠቅማችሁ አያይዙ ይላል፡፡ አጣማሪዎቹ መቅረብ የነበሩት በአረፍተ ነገሮቹ ትይዩ ሳይሆን ለብቻቸው ነበር፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች አረፍተ ነገሮቹን ስያጣምሩ በአረፍተ ነገሩ ትይዩ ካለው አጣማሪዎች ጋር ይሁን ከቀረቡት መርጠው ግልፅ ባለመሆኑ ሊያወዛግባቸው ይችላል። በመሆኑም ተማሪዎች መልመጃው የቀረበበትን ሁኔታ ስመለከቱ ግራ የመጋባት ሁኔታ ስለሚገጥም አሻሚነት አለው።

*እንዲሁም "ከሚከተሉት ቃላት ለመጥራት የሚያስቸግሯችሁ ድምጾች ያሉባቸው ቃላት እየመረጣችሁ በመምህራችሁ እየታገዛችሁ በትክክል ለመጥራት ሞክሩ" /ገጽ 63/*

ይህንን የሰዋስው ትምህርት ይዘት ስንመለከት ቋንቋዉ ለተማሪዉ ሁለተኛ እንደመሆኑ አንዳንድ የቋንቋዉን ድምጾች ለመጥራት እንደሚቸገሩ ትምህርት ስድስት ላይ ተጠቅሷል። ድምጾችን በአግባቡ ያለመጥራት ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ ለቃሉ ትክክለኛ ትርጉም ከመስጠት ይልቅ ወደተሳሳተ ፍቺ ሊያሸጋግር ይችላል። በተለይ በአዳምጦ መረዳት ትምህርት ጊዜ የቃሉን ትርጉም ተማሪው ሊያዛባ እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ተማሪዎችም በታላሚ ቋንቋ ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ይሁን በሌላ ምክንያት ለመጥራት የሚያስቸግሩ ድምጾችን አጠራር በመምህሩ መሪነት ወይም አጋዥነት ቀስ በቀስ በሂደት እንዲለምዱ የሚያደርግ ነው።

ስለሆነም እነዚህን ለመጥራት የሚያስቸግሩትን ድምጾች በሂደት በመምህሩ እርዳት ቀስ በቀስ አስተካክለዉ እንዲጠሩ ለማስቻል የቀረበ በመሆኑ በሂደት ተኮር የቀረበ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው "አካል ጉዳተኛ" በሚል ርዕስ ማዳመጥን ለማስተማር በተዘጋጀ ትምህርት ስር *"ባዶ ቦታ አሟሉ"* በሚለው የቀረበ የሚከተለውን እናገኛለን።

*ቀጥሎ የቀረበው የተጓደለ ጽሐፍ፣ መምህሩ በንባብ በሚያስደምጧችሁ ጽሐፍ መሰረት የሚመለስ ነው። ከማዳመጣችሁ በፊት የተጓደለውን ሀሳብ የያዙትን አንቀጾች አንብባችሁ ምን ዓይነት መረጃዎች ላይ ማተኮር እንደሚገባችሁ ለይታችሁ አሟልታችሁ ጻፈ /ገጽ 80/*

ከዚህ አቀራረብ ሁለት ነገሮችን መረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች የተጓደለውን ቦታ እንዲያሟሉ ያስችላቸው ዘንድ ምንባብ በመምህሩ ይቀርባል፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ባዶ ቦታውን በቀላሉ የሚያሟሉበትን መንገድ ያገኛሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በመምህሩ ምንባቡ ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎች የተጓደሉ ዓረፍተ ነገሮችን አሰቀድሞ በማንበብ የራሳቸውን ግምት ያሰቀምጡና ቀጥሎ ምንባቡ ስቀርብ ቀድመው ያስቀመጡት መልስ ትክክል መሆን አለመሆኑን እያስተካከሉ ይሄዳሉ፡፡ በዚህ መሰረት በሂደት የተጓደሉ አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላትና ሐረጋት አሟልተው እንዲያቀርቡ የሚያስችል በመሆኑም በሂደት ተኮር አቀራረብ ስልት የቀረበ ነው ማለት ይቻላል፡፡

#### 4.1.4.2 በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ

በዚህ ክፍል ደረጃ የተካተቱ በርካታ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሂደት ተኮር አቀራረብ ስልት የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህም ጠቅለል ባለመልኩ በሶስት አብይ ሰዋስው ትምህርት ስር ልጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው በገጽ 6፣ 17፣ 18፣ 25፣ 47፣ 49፣ 56፣ 75 እና 93 የሚገኙት በስነ-ፍች ዙሪያ  የሚያተኩሩ ሲሆን ቃላትን በተለያዩ መልኩ አቅርበው ፍቺ ስጡ የሚሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው በስነ-አገባብ ዙሪያ የሚያተኩር ሲሆን በገጽ 6፣ 40፣ 41፣ 42፣ 53፣ 54፣ 62 እና 82 ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ ተማሪዎች አረፍተ ነገርን በተለያዩ መንገድ እንዲመሰርቱ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ከአያያዥ ቃላት (አጣማሪዎች) ጋር የተያያዙ ይዘቶች ሲሆኑ በገጽ 97፣ 98 እና 103 ላይ ይገኛሉ፡፡

በስነ-ፍቺ አብይ ስዋስው ትምህርት ይዘት ዙሪያ ለቃላት ፍቺ መስጠት ላይ የሚያተኩረው ይዘት አብዛኛው በአውድ ታግዞ መስጠቱ ተማሪዎቹ ለቃላቱ ፍቺ በቀላሉ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃላቱንና የቃላቱን ፍቺ በተለያዩ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የቋንቋውን ስርዓት በተናጠል ሳይሆን በአውድ ታግዘው በመማር ወደተፈላጊው ቋንቋ ግብ እንዲደርሱ ስለሚያስችላቸው እንደጠንካራ ጎን ሊጠቀስለት ይችላል፡፡

በገጽ 25 እና 93 ላይ ቃላትን ዘርዝረው ፍቺ ተናገሩ ከሚለው ትዕዛዝ ውጪ ሌሎቹ በአውድ የታቀፉ ናቸው፡፡ በመሆኑ የቃላት ትምህርት በተናጠል ከሚሰጥ ይልቅ በአውድ ታግዞ ብቀርብ ጥሩ ውጤት ይኖረዋል፡፡

ሌላው በስነ-አገባብ ዙሪያ የቀረበው ሰዋስው ትምህርት ይዘት ተውላጠ ስምን፣ ተውሳከ ግስን፣ የመሆንና የድርጊት ግስን በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመርቱ የሚያዝ ነው፡፡ ትዕዛዙ

ተማሪዎች አረፍተ ነገሮችን ቃላት ከራሳቸው አፍልቀው እንድመሰርቱ የሚያዝ ነው፡፡ እነዚያ ለአረፍተ ነገሩ ምስርት የተጠቀሙት ቃላት የቃል ክፍላቸው የትኛው እንደሆነ ይለያሉ፡፡ አረፍተ ነገሩን ስመሰርቱም ቃላቱ በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን ሙያ ምን እንደሆነ ለይተው እንዲመሰርቱ የሚያስችልም ነው፡፡ በመሆኑም አቀራረቡ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ተማሪዎች በሂደት እንዲያከናውኑ የሚያዝ በመሆን በሂደት ተኮር የቀረበ ነው፡፡

በአረፍተ ነገር ውስጥ ስም የባለቤትነት፣ የተሳቢነትና የዘርፍነት ሙያን ይወጣል፡፡ ከእነዚህ መካከል በገጽ /53/ ላይ ስም የባለቤትነትና የተሳቢነት ሙያ የሚወጣ መሆኑን ለይተው ተማሪዎች አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያዘው ትዕዛዝ በሂደት ተኮር ዘዴ የቀረበ ይዘት መሆኑንም መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘት አደረጃጀት

### 4.2.1 ተከታታይነት

በክለሳ ድርሳን ክፍል እንደተጠቀሰው "ተከታታይነት" በአንድ ክፍል ደረጃ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመው መደራጀታቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ክትትሎሽ ስንፈትሽ የተወሰኑ ይዘቶች ተከታትለው ተደራጅተው እናገኛለን፡፡ ክትትሎሹ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ትምህርት ይዘቱን በቀላሉ እንዲረዱና እንዲያስታዉሱ የሚያግዝ አደረጃጀት ነው፡፡ በተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በተሻለ ደረጃ ክትትሎሽ አግኝተው የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

**ሰንጠረዥ 3.** በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ ሁኔታ

| የሰዋስው ትምህርት ይዘት | | ደግግሞሽ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | የሚገኝበት ገጽ |
| ስነ-ድምጽ | የድምጽ ጥብቀትና ልለት | 3 | 30፣62፣63 |
| ስነ-ምዕላድ | የቃል ክፍሎችን መለየት | 2 | 41፣42 |
| | ምዕላዶችን ማጣመርና መነጠል | 3 | 24፣25፣26 |
| ስነ-ፍቺ | ለቃላት ፍች መስጠት | 7 | 10፣12፣24(2 ጊዜ)፣36፣ 37፣46 |
| ስነ-አገባብ | አረፍተ ነገር | 7 | 13፣16፣27፣49፣50፣53፣80 |
| | ስማዊና ግሳዊ ሀረግ መለየት | 2 | 51 |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደምንመለከተው በተተኳሪ 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ስድስት የሚሆኑት ሁለት እስከ ሰባት ጊዜ ተደጋግመዉ ተደራጅቷል፡፡ ከነዚህ መካከል "የቃል ክፍሎችን መለየት" እና "ስማዊና ግሳዊ ሀረግ መለየት" የሚሉት ሁለት ጊዜ ብቻ ተደጋግመዋል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ይዘቶች ሁለት ጊዜ ብቻ ብደጋገሙም አንድ ጊዜ ብቻ ታይተው የጠፉ በርካታ ሰዋስዋዊ ትምህርት ይዘቶች በመኖራቸው የተሻሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ሌሎቹ ሶስት እስከ ሰባት ጊዜ ድረስ ተደጋግመው መደራጀታቸውን ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡ የድግግሞሽ ሁኔታውም ባንድ ትምህርት ይዘት ስር አልያም በተከታታይ ገጽ ሁለት ጊዜ ብቅ ብለው ሲጠፉ እናገኛቸዋለን፡፡

የተሻለ በሚባል ደረጃ ተከታትለው የተደራጁት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለቃላት ፍቺ መስጠት የሚሉትና ከአረፍተ ነገር ጋር የተያያዙ ይዘቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ሰባት ጊዜ ተደጋግመው እናገኛለን፡፡ በተለይ ከአረፍተ ነገር ጋር ተያይዞ የተደራጀውን ስንመለከት ተማሪዎች በጅምር የቀረቡ አረፍተ ነገሮች ሀሳብ ከራስ አፍልቀው ማሟላት እንዲችሉ፣ ከአረፍተ ነገር ውስጥ ሰዋስዋዊ ስህተትን ለይተው እዲያስተካክሉ እንዲሁም አያያዥ ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን እንዲያይዙ ለማስቻል የታለሙ ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 4.** በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ ሁኔታ

| የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | የሚገኝበት ገጽ |
| ስነ-ምዕላድ | ቃላትን በምዕላድ መነጣጠልና ምዕላዶችን ማጣመር | 2 | 30 |
| | ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ | 4 | 43፣80፣82(2x) |
| | የቃል እርባታ | 2 | 51 |
| | ጾታ አመልካች ያላቸውና የሌላቸውን ስሞች ለዩ | 2 | 51፣54 |
| | ግሶችን ከጊዜ አንጻር መለየት | 3 | 53፣ 53፣ 54፣ |
| | የቃል ምስረታ | 2 | 61፣63 |
| ስነ-አገባብ | ስማዊና ግሳዊ ሀረግ መለየት | 3 | 11፣81፣83 |
| | አረፍተ ነገር | 16 | 7፣8፣40(2x)፣41፣42፣53፣54፣63(2x)፣82(2x)፣97(3x)፣103 |
| ስነ-ፍቺ | ለቃላት ፍቺ መፈልግ | 10 | 6፣17፣18፣25፣29፣47፣49፣56፣75፣93 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደምንመለከተው በ8ኛ ክፍል *መማሪያ* መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል ዘጠኝ የሚሆኑት ሁለት እስከ አስራ ስድስት ጊዜ ተደጋግመዉ ተደራጅተዋል፡፡ በተተኳሪዉ *መማሪያ* መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የድግግሞሽ መጠን የሚታይበት በስነ-አገባብ ዙሪያ የቀረበዉ "አረፍተ ነገር" የሚለው እና በስነ-ፍቺ ዙሪያ የቀረበው *"ለቃላት ፍቺ ፈልግ"* የተባሉት ሲሆን ይዘቶቹ እያንዳንዳቸዉ በተከታታይ አስራ ስድስት እና አስር ጊዜ ተደጋግመው ተደራጅተዋል፡፡

ቃላትን በምዕላድ መነጣጠልና ምዕላዶችን ማጣመር፣ የቃል እርባታ፣ ጾታ አመልካች ያላቸውና የሌላቸውን ስሞች መለየት፣ የቃል ምስረታ የተባሉት ደግሞ ሁለት ጊዜ ብቻ የተደገሙ ቢሆኑም በዚህ ክፍል ደረጃ አንድ ጊዜ ብቻ ታይተው የጠፉ ሌሎች ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስለሚገኙ ሁለት ጊዜ መደገም ትንሽ አይደለም፡፡

ሌላው ግሶችን ከጊዜ አንጻር መለየት የሚለው እና ስማዊና ግሳዊ ሀረግ መለየት የተባሉት ደግሞ እስከ ሶስት ጊዜ፤ እንዲሁም ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ የተባለው ደግሞ አራት ጊዜ ተደግመው ተደራጅተዋል፡፡

በስነ-ፍቺ ትምህርት ዙሪያ ለቃላት ፍቺ ፈልጉ በሚል ርዕስ የተደራጀው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ማለትም "ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ፣ ተቃራኒ ፍቺ፣ አገባባዊ ፍቺ፣ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ፣ እንዲሁም አውዳዊ ፍቺ ስጡ" በሚል ቃላቱን በተናጠል አልያም በአዛምድ መልክ ከአውድ ነጥለው፤ አንዳንድ ጊዜ እንደሚደረገው በምንባብ ውስጥ አምጠተዋል፡፡ ከአውድ ውጪ የሚቀርብ የቃል ትምህርት ፋይዳው የጎላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ተማሪው ለቃላቱ በተጠየቀው መሰረት ፍቺ ከመስጠት በዘለለ ቃላቱን ለተግባቦት ወይም በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ የሚጠቀምበት ሁኔታ እጅግ ዝቅተኛ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የቃል ትምህርት በተናጠል ሳይሆን በምንባብ አልያም በአውድ ውስጥ መቅረብ ተገቢ ነው፡፡

በተለይ ኢ-አፍ ፈት ለሆኑ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ድግግሞሽ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርጽና ስርዓት በቀላሉ ለመረዳት ሊያዳግታቸው ስለሚችል፡፡ ተተኳሪ መጽሐፉ ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ደግሞ የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት በቀላሉ ለይተዉ ላያውቁ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት ለይተዉ አዉቀዉ እንዲገለገሉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ተደጋግመዉ መደራጀቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪ *መማሪያ* መጽሐፍ ውስጥ ይህ ጉዳይ

በጥቂት ጉዳዮች ላይ ካልሆነ በስተቀር ትኩረት አልተሰጠም ማለት ይቻላል። ተከታትለዉ ተደራጅተዋል ተብለዉ የተዘረዘሩትም ይዘቶቹን ለማስተማር ባቀረቡበት በዚያዉ ገጽ እና አልፎ አልፎ ደግሞ በተከታታይ ገጽ ላይ የተደራጁ ናቸው እንጂ ስለ ይዘቶቹ "ተከታታይነት" ጉዳይ ግድ ብሏቸው ያደራጁት አይደለም።

### 4.3.2 ተለጣጣቂነት

በክለሳ ድርሳን ክፍል እንደተገለጸው ተለጣጣቂነት ለደረጃው በተዘጋጁ *መማሪያ መጽሐፍት* ውስጥ የተካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ባንድ ክፍል ደረጃ ይሁን በሌሎች ክፍል ደረጃዎች ሲደራጁ ተከታትለው በመምጣት ስፋትና ጥልቀቱ እየጨመረ እንዲሁም *መጀመሪያ* ከመጣው ቀጥሎ የሚመጣው ለውጥ እያሳየ *መደራጀቱን* የሚመለከት ነው። ከዚህ አኳያ ተተኳሪ *መማሪያ መጽሐፍት* ውስጥ “በአረፍተ ነገር” ዙሪያ የሚያተኩረውን ይዘት መጥቀስ ይቻላል። የጥናቱ ታላሚ በሆነው *መማሪያ መጽሐፍ* ውስጥ ድግግሞሽ አግኝተዉ ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በ7ኛ ክፍል “*አረፍተ ነገር*” ላይ ያተኮሩ ናቸው። ትዕዛዞች በመጥቀስ እንደሚከተለው እንመልከት።

1. *ቀጥሎ የተሰጡትን አረፍተ ነገሮች ነጠላ ወይም ድርብ ዐረፍተ ነገር በማለት ለዩ (ገጽ 27)*
2. *ስለ ነጠላና ድርብ አረፍተ ነገር አመሰራረት በተማራችሁት መሰረት አራት ነጠላ አረፍተ ነገሮችንና አራት ድርብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱና ለመምህራችሁ አሳዩ (ገጽ 27)*
3. *ቀጥሎ በሰንጠረዡ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች ከተሰጡት አጣማሪዎች (አያያዦች) ተገቢውን በመጠቀም የተሟላ ሀሳብ መስርቱ* (ገጽ 49)
4. *የተለያዩ አያያዦችን (አጣማሪዎችን) በመጠቀም አምስት አረፍተ ነገሮችን መስርቱና ለመምህራችሁ አሳዩ* (ገጽ 50)
5. *ከዚህ ቀጥል የቀረቡት አረፍተ ነገሮች የሰዋስው (የመዋቅር) ስህተት ያሉባቸው ናቸው። አረፍተ ነገሮቹን በጥንቃቄ አንብባችሁ ስህተቱን በመለየት አስተካክላችሁ ጻፉ* (ገጽ 53)

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ትዕዛዞች እንደሚያሳዩት ሊተላለፍ የተፈለገው የትምህርቱ ዋና ትኩረት የአረፍተ ነገር አመሰራረት፣ አይነትና ሰዋስዋዊነት ላይ ነው። ይህም አረፍተ ነገሮችን ነጠላና ድርብ ብለው ከለዩ በኋላ ድርብና ነጠላ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ፣ በአያያዥ ቃላት አማካኝነት ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ድርብ አድርገው እንዲመሰርቱ ለማስቻል፤ አያያዦችን በመጠቀም ከራሳቸው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የተደራጁ ናቸው። በመጨረሻም የመሰረቷቸውን አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ማለትም አረፍተ ነገሮቹ የቋንቋውን አረፍተ ነገር አወቃቀር ስርዓት በብቀው መዋቀራቸውን እያረጋገጡ ወደተፈላጊው ስርዓት እንዲደርሱ

ለማስቻል የተደራጁ ናቸው ማለት ይቻላል። በመሆኑም ሂደቱ እንደ ጠንካራ ጎን ሊታይለት የሚችል ነው።

በተመሳሳይ መንገድ በተተኳሪ 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተለጣጣቂነት አግኝተው የተደራጁ ይዘቶች በ"አረፍተ ነገር" ላይ የሚያተኩር ሆኖ እናገኛለን።

1. *የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች ተጠቅማችሁ የራሳችሁን አረፍተ ነገሮች መስርቱ (ገጽ-41)፣*
2. *ከመሆን ግሶች ሁለቱን፣ ከድርጊት ግሶች ሁለቱን በመጠቀም የራሳችሁን አረፍተ ነገር ጻፉ (ገጽ-42)፣*
3. *ጊዜ አመልካች ግሶችን ከአሁን፣ ከሀላፊና ከወደፊት ጊዜ አንጻር በሶስት አረፍተ ነገሮች እየተጠቀማችሁ ስሩ (ገጽ-54)፣*
4. *ቀጥሎ የቀረቡላችሁን ዓ.ነገሮች አዎንታዊና አሉታዊ በማለት ለዩ (ገጽ-62)፣*
5. *ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት አስር አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮች መስርቱ (ገጽ-63)፣*
6. *ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ያላቸው አረፍተ ነገሮችን መስርቱ (ገጽ-82)፣*
7. *ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች ተጠቅማችሁ ዓ.ነገሮቹን አሟሉ (ገጽ 97)፣* የሚሉት ተጠቃሽ ናቸዉ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ትዕዛዞች እንደሚያመለክቱት ሊተላለፍ የተፈለገዉ የትምህርቱ ዋና ዓላማ ተማሪዎች አረፍተ ነገርን ከቃል ክፍሎች ተዉሳከ ግስን እና ግስን(መሆን ግስ፣ ድርጊት ግስ፣ ጊዜ አመልካች ግስ(የአሁን ጊዜ ግስን፣ ኃላፊ ጊዜ ግስንና የወደፊት ጊዜ ግስን)) ተጠቅመው የራሳቸውን አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ነው። እዚህ ክፍል ላይ ተማሪዎች ከቃል ክፍሎች ተውሳከ ግስንና ግስን በመጠቀም ዓ.ነገሮችን እንዲያዋቅሩ የተደረገበት መንገድ ተለጣጣቂነት ኖሮት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በተለይ ግስ በውስጡ ሰፊ ምድብ ያለው መሆኑን እየተረዱ አረፍተ ነገሮችን እንዲያዋቅሩ መደረጉ የይዘቱን ጥልቀትና ስፋት ተማሪዎች እንዲረዱ ለማስቻል የታለመ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሌላው ደግሞ የተመሰረቱ አረፍተ ነገሮችን አሉታዊና አዎንታዊ እያሉ ከለዩ በኂላ የራሳቸዉን አሉታዊና አዎንታዊ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የተደራጀ ይዘትም ተጠቃሽ ነው። ይህ ደግሞ አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ውስብስብ እያደገ መምጣቱ የሚያመላክት ነው። ከሀረግ አይነቶች ስማዊና ግሳዊ ሀረግን እና አያያዦችን በመጠቀም የተደራጀውን ይዘትም ለተለጣጣቂነቱ ማሳያ ነው ማለት ይጫላል።

እነዚህ ይዘቶች ከዚህ ቀደም እንደሚደረገው ሁሉ ምንም አይነት ዝርዝር ትዕዛዝ ሳይሰጣቸው በደፈናው አረፍተ ነገር መስርቱ እያሉ ከማቅረብ ይልቅ ተማሪዎች የሚመሰርቷቸው አረፍተ ነገሮችን ከየትኛው ግስ፣ ከአይነቶቹ የትኛውን እንደመሰረቱ፣ ባለቤቱና ማሰሪያ አንቀጹ ክፍል በወጉ መኖሩን፣ በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ተገቢ አያያዥ መጠቀማቸውን በጥልቀት እየለዩ እንዲሄዱ የሚያደርግ በመሆኑ ከተለጣጣቂነት ባህሪ አንጻር እንደ ጠንካራ ጎን ሊታይለት የሚችል ነው ማለት ይቻላል።

ተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍት ተመሳሳይ ይዘት ላይ የሚያተኩሩ በርካታ ጉዳዮች ብኖሩም የአደረጃጀት ለውጥ ሳይታይባቸው፣ ስፋትና ጥልቀት ሳይኖራቸው የተደራጁ ይዘቶችም እንዳሉ በጥናቱ ተደርሷል። ለምሳሌ በ8ኛ ክፍል ገጽ 81 ና 83 ላይ ስለ ሀረግ የተነሳውን ትዕዛዝ እንመልከት።

*"ከዚህ በታች የተሰጧችሁን አረፍተ ነገሮች ስማዊና ግሳዊ ሀረግ ለይታችሁ ጻፉ /ገጽ 81/"* ከሚለው ጋር ምንም ልዩነት የለሌው በዚያው ክፍል ደረጃ ገጽ /83/ ላይ *"ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎችን ለይታችሁ አውጡ"*

*ምሳሌ፡- እሷ የኔ የክፍል ጓደኛዬ ናት።*

*ስማዊ ሀረግ- እኔ*

*ግሳዊ ሀረግ- የእኔ ክፍል ጓደኛዬ*

የትምህርቱ ዓላማ አረፍተ ነገሮችን በሀረግ እንዲከፍሉ ለማስቻል የታለመ ብሆንም ይዘቶቹ ምንም አይነት የአደረጃጀት ለውጥ ሳይታይባቸው ቀርበው እናገኛለን። ይህ ጉዳይ ስለተለጣጣቂነት ታሳቢ ተደርጎ የተደራጀ አይመስልም። ምክንያቱም ባንድ ምዕራፍ ውስጥ ተቀራራቢ ገጽ ላይ መምጣቱ ለይዘቱ ተለጣጣቂነት ትኩረት የተሰጠ አይደለም ሊያስብለው ይችላል።

ሌላው በ8ኛ ክፍል በ"ቃላት ፍቺ" ላይ የሚያተኩ ምንም ለውጥ ሳያሳዩ ተደጋግመው የተደራጁ የሚከተሉትን እናገኛለን።

1. *ቀጥሎ ለተዘረዘሩ ቃላት አውዳዊ ፍች ፈላጉ /ነጽ* 6/
2. *ተማሪዎች ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ፍች ተናገሩ /ነጽ 25/*
3. *ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ /ነጽ 47/*

4. *ከላይ ያለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ /ገጽ 49/*
5. *ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ጻፉ /ገጽ 56/*
6. *ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ቃላት ፍች ገምቱ /ገጽ 93/*

እዚህ ክፍል ላይ ሊተላለፍ የተፈለገው የትምህርቱ ዓላማ ተማሪዎች አውድን በመጠቀም ለቃላት ፍች እንዲሰጡ ለማስቻል ነው። ይሁን እንጂ ከላይ በትዕዛዞቹ ላይ እንደምንመለከተው ተማሪዎች ለቃላቱ ፍች እንዲሰጡ የተደረገበት መንገድ ተመሳሳይ ነው። ይህ ደግሞ ስለተለጣጣቂነት ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ያሳያል።

## 4.3 መማሪያ መጻሕፍቱ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ተዛምዶ

**ሰንጠረዥ 5.** ተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍት ከደቡብ ክልል ትምህርት ብሮ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና

| የክፍል ደረጃ | በመማሪያ መመጻሕፍቱ የቀረቡ ዝርዝር ሰዋስው ይዘቶች | በመርሃ ት/ቱ ውስጥ | በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ |
|---|---|---|---|
| በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ | ለቃላት እንደ አገባባቸው ተመሳሳይ ፍች መስጠት | √ | √ |
| | የቃላት ተቃራኒ ፍች | √ | √ |
| | ቃላትን በትክክል መጥራት | √ | √ |
| | የድምፅ ጥብቀትን መለየት | √ | √ |
| | የቃል ክፍሎችን መለየት | √ | √ |
| | የቃል ክፍሎችን ከዓ.ነገር ውስጥ መለየት | √ | √ |
| | ጅምር ዓ.ነገሮችን አሟልቶ መጻፍ | √ | √ |
| | የተጓደሉ ቦታዎችን በተገቢ ቃላት ማሟላት | √ | √ |
| | ምዕላዶችን በማጣመር ቃላትን መመስረት | √ | √ |
| | ቃላትን በምዕላድ መነጣጠል | √ | √ |
| | አረፍተ ነገሮችን ነጠላና ድርብ እያሉ መለየት | √ | √ |
| | ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | √ | √ |
| | ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | √ | √ |
| | አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ዓ.ነገሮችን መመስረት | √ | √ |
| | የዓ.ነገር ክፍሎችን መለየት | √ | √ |
| | ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በዓ.ነገር ውስጥ መጠቀም | √ | √ |
| | ሰወስዋዊ ስህተቶችን ከዓ.ነገር ውስጥ መለየት | √ | √ |
| | ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት | √ | √ |
| | ለቃላት ተቃራኒ ፍች መስጠት | √ | √ |
| | ቃላትን ከተመሳሳይ ፍች ጋር ማዛመድ | √ | √ |
| | ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍች መስጠት | √ | √ |
| | ቃለቀትን በምዕላድ መነጣጠል | √ | √ |
| | ምዕላዶችን ማጣመር | √ | √ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ | የዓ.ነገርን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ መለየት | √ | √ |
| | ጅምር አረፍተ ነገሮችን ማሟላት | √ | √ |
| | የቃላትን መሰረት በመለየት ቃላትን መመስረት | √ | √ |
| | ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ | √ | √ |
| | የስሞችን ዋና ቃል መለየት | √ | √ |
| | ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን መለየት | √ | √ |
| | ነጠላ ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር መለወጥ | √ | √ |
| | ብዙ ቁጥር ስሞችን ወደ ነጠላ ቁጥር መለወጥ | √ | √ |
| | ጾታ አመልካች ቅጥያዎችን መለየት | √ | √ |
| | ጾታ አመልካች የሌላቸው ስሞችን መለየት | √ | √ |
| | በአረፍተ ነገር ውስጥ የስም ሙያን መለየት | √ | √ |
| | የጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን መለየት | √ | √ |
| | አዎንታዊና አሉታዊ ዓ.ነገሮችን መለየትና መመስረት | √ | √ |
| | የዓ.ነገር ክፍሎችን መለየት(ስማዊና ግሳዊ ሀረግ) | √ | √ |
| | ሰዋስዋዊ ዓ.ነገሮችን መመስረት | √ | √ |
| | አያያዦችን በመጠቀም ዓ.ነገሮችን መመስረት | √ | √ |
| | አያያዦችን ከዓ.ነገር ውስጥ መለየት | √ | √ |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከመርሃ-ትምህርት አንጻር ዝምድና ኖሯቸው የተዘጋጁ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ አስቀድሞ በመማሪያ መጽሐፍቱ መግቢያ ላይም መማሪያ መጽሐፍቱ የእርከኑን መርሃ ትምህርት መሰረት አድርገው እንደተዘጋጁም ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም ይህ ደግሞ እንደጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ነው፡፡

በመረጃ ትንተና ክፍል የየክፍል መማሪያ መጽሐፍት ቅኝት ተደርጎ በ7ኛ ክፍል 25(ሃያ አምስት)፣ በ8ኛ ክፍል ደግሞ 44(አርባ አራት) የሚሆኑ የሰዋስው መልመጃዎች ተገኝተዋል፡፡ ከላይ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ግን የእነዚያ ድምር ውጤት ላይመጣ ይችላል፡፡ ይህ የሆነበት አንዳንድ ይዘቶች የተደጋገሙ፣ የተወሰኑት ደግሞ ሳይደጋገሙ በመምጣታቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ነው፡፡

ጥናቱን ከዳር ለማድረስ ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ቃለ-መጠይቅን እንደ አጋዥ መረጃ መሰብሰቢያ ተጠቅሜ የእርከኑን ክፍል ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህራን ቃለ-መጠይቅ ባቀርብም በቂ የሆነ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ክፍል በተጠቀሰው ንድፈ ሃሳባዊ ብያኔዎችና አጠናን ዘዴ መሰረት ግምገማ ተደርገዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ምርምር ዘዴን በመከተል በሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች በገላጭ ስልት ተተንትነዋል፡፡

በመርሃ ትምህርቱ ላይ የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፉ በ39 ሳምንት፤ በ78 ክፍለ ጊዜ እና በ52 ሰዓት እንደሚጠናቀቅ (አጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፤ “ቅድመ አንደኛ- ሁለተኛ ደረጃ” መስከረም 2015፣24) አስቀምጧል፡፡ ነገር ግን አዘጋጆቹ መማሪያ መጽሐፉ በ48 ሳምንት፤ በ96 ክፍለ ጊዜ እና በ64 ሰዓት እንዲጠናቀቅ አድርገው አዘጋጅተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በሁለቱ መካከል የዘጠኝ (9) ሳምንት፤ አስራ ስምንት(18) ክፍለ ጊዜ እና አስራ ሁለት(12) ሰዓት ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ የሚያሳየው የመጽሐፉ አዘጋጆች መርሃ ትምህርቱ ላይ የዓመቱ ትምህርት ምን ያህል ጊዜ ልፈጅ እንደሚችል የተቀመጠውን ሳይመለከቱ ማዘጋጀታቸውን ነው፡፡

አስቀድሞ በመለስተኛ አንደኛ ደረጃ ማለትም ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሚኖራቸው የትምህርት ጊዜ አስር ወር ሲሆን ሰላሳ ዘጠኝ ሳምንት እንዳለቸው፣ የቋንቋ ትምህርት ደግሞ በሳምንት ሁለት ጊዜ እንደሚሰጥ (አጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ (ቅድመ-አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ) መስከረም 2015: 24) ሃሳባ ላይ በተካሄደው የትምህርት ጉባኤ ሰነድ ላይ ይደነግጋል፡፡

በዚህ የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፉ የአመቱን ትምህርት ጊዜ ስናሰላ በ39 ሳምንት፤ በ78 ክፍለ ጊዜ እና በ52 ሰዓት እንደሚጠናቀቅ የተዘጋጀ ቢሆንም አዘጋጆቹ መጽሐፉን በአርባ ሰባት

ሙሉና ከአርባ ስምንተኛው ሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ (47 ½)፣ በዘጠና አምስት(95) ክፍለ ጊዜ እና በስልሳ ሶስት(63) ሰዓት ከአርባ ደቂቃ(40) እንዲጠናቀቅ አድርገው አዘጋጅተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ከቀረበው ውጪ ስምንት ሙሉ ከዘጠነኛው ሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ (8 ½) ሳምንት፤ አስራ ሰባት(17) ክፍለ ጊዜ እና አስራ አስራ አንድ ሰዓት ከአርባ ደቂቃ(11፡40) ሰዓት ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ በመጻሐፉ አዘጋጆቹና በመርሃ ትምህርቱ መካከል ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡

ሌላው በመማሪያ መጽሐፎቹ የተካተቱ ሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ስንመለከት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መርህ ተከትሎ የተዋቀሩ እና ሂደት ተኮር አቀራረብ መርህ ተከትሎ የቀረቡ ይዘቶች አብዛኛውን ክፍል የያዙ ሲሆን የተወሰኑ ሰዋስው ይዘቶች በውጤት ተኮር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ መርህ ተከትለው መቅረባቸውን ከሰነድ ፍተሻው ለማግኘት ተችሏል፡፡

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መርህ ተከትለው በቀረቡ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ዙሪያ አንዳንድ ገለጻዎችና ምሳሌዎች በበቂ ሁኔታ ተብራርተውና ግልጽ ሆነው የቀረቡ ሳይሆኑ የግልጽነት ችግር ያሉባቸው መሆኑን ከሰነድ ፍተሻው ለማግኘት ተችሏል፡፡

ከአደረጃጀት አንጻር በተተኳሪ 7ኛና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተደራጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ ተከታታይነት አግኝተው የተደራጁ ሲሆን ስለተከታታይነታቸው ትኩረት ሳይሰጣቸው ባንድ ትምህርት ይዘት ስር አልያም በተከታታይ ገጽ ተደጋግመው ሲደራጁ ይስተዋላሉ፡፡ "ዓ.ነገር" ላይ የሚያተኩረው ይዘት ተለጣጣቂነትን ጠብቆ መደራጀቱን ከጥናቱ ለማግኘት ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ ተተኳሪዎቹ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ በተደረገው ግምገማ በመጽሐፎቹ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡

ከጠንካራ ጎኖች ስንነሳ ምንም እንኳን ይዘቶቹ ሚዛናዊና ተመጣጣኝ ባይሆኑም ሁሉንም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መንገዶችን አካተው መያዛቸው፤ መርሃ ትምህርት መሰረት አድርገው መዘጋጀታቸው፣ የተማሪውን ዳራ ወይም የመጡበትን አውድ መነሻ ያደረጉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካተቱ፣ ወዘተ በጠንካራ ጎን የታዩ ይዘቶች ናቸው፡፡

በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ በተካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ እንደ ደካማ ጎን የታዩት የቃላት ትምህርት ከአውድ ውጪ መሰጠት፣ አንዳንድ መመሪያዎችና ይዘቶች ግልጽ አለመሆን፣ የተወሰኑ ይዘቶች መቅረብ የሚገባው መርህ እያለ ያለብስለት መቅረብ፣ የይዘቶቹ አቀራረብም ሆነ አደረጃጀት እኩል ተመጣጣኝ ያለመሆን፣ ድግግሞሽ አግኝተው የተደራጁ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሁሉም ምዕራፎች እና ክፍል ደረጃዎች ተከታትለው ያለመደራጀት፣ ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

## 5.2 አስተያየት

በዚህ ጥናት ውስጥ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ደካማ ጎኖች ደግሞ እንዲሻሻሉ የሚከተሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተሰንዝረዋል፡፡

- የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስደራጁም ሆነ ስቀርቡ በተወሰኑ አደረጃጀትና አቀራረብ መርህ ላይ ብቻ ሳይወሰኑ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ብቀርቡ፣
- የሰዋስው ይዘቶች ስቀርቡም ሆነ ስደራጁ አሻሚ የሆኑ ትዕዛዞች እንዳይኖሩ መጠንቀቅ፣
- ግልጽ ያልሆኑ ገለጻዎችና ምሳሌዎች እንዳይካተቱ ትኩረት መስጠት፣
- የቃላት ትምህርት ከአውድ ውጪ ተነጥለው ለብቻ መሰጠቱ ተማሪዎቹ የቃላቱን ትርጉም ሸምድደው በማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ለመጠቀም አሰቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን በአውድ ብታቀፉ፣
- የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተወሰኑ ምዕራፎች ላይ በዛ ብለው ከመምጣት ይልቅ እኩል ሚዛናዊ በሆነ መልኩ በየምዕራፉ ብቀርቡ፣
- ይዘቶቹ በተወሰነ ቦታ፣ በተከታታይ ገጽና ምዕራፍ ብቻ ተከታትለው ከመቅረብና ከመደራጀት ይልቅ ስለ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ጉዳይ ትኩረት ብሰጠው፣
- የመጽሐፉ አዘጋጆችና አሻሻዮች በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ በሚካተቱ ሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ በየጊዘው የሚደረጉ ጥናቶችን ተመልክተው ብያዘጋጁ፣
- የመምህሩ መምሪያ ሲዘጋጅ ከተዘጋጀለት የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ጋር መጣጣሙን አዘጋጆች ማረጋገጥ ያሰፈልጋል፣
- በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚቀርቡ ሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችን በሚገባ ገምግመው ከተማሪው ፊላጎትና ከትምህርቱ ዓላማ ጋር አዛምዶ ለማዘጋጀት ለስርዓተ ትምህርትና መጽሐፍ አዘጋጆች፣ ለትምህርት ባለሙያዎች፣ ለቋንቋ መምህራን ተከታታይ የሆነ ስልጠና ብሰጥ፣ የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡

## ዋቢ ጽሐፎች


ሐዋዝ ወልደየስ (2000) "በአዲስ አበባና በአማራ ክልል አንደኛና ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ንጽጽራዊ ትንተና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ በከፊል የማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ሰሚራ አሊ (2010) "በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ በከፊል የማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ባየ ይማም (2000) <u>የአማርኛ ሰዋሰው።</u> የተሻሻለ ሁለተኛ ዕትም፤ አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ኃ.የተ.የግ.ማህበር።

-------------(2002) <u>አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።</u> አዲስ አበባ፣ አልፋ ማተሚያ።

ባዬ ተሾመ (2004) "በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ በከፊል የማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)።

ተስፋዬ በቀለ (1993) "በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ በከፊል የማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)።

ዘላለም ጌታቸው (1998) <u>መሰረታዊ የቋንቋ መርሃ ትምህርት፣ መማሪያ መጽሐፍና ፈተና አዘገጃጀት መርሆች።</u> አዲስ አበባ።

የአጠቃላይ ትምህርት ስርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ (ቅድመ-አንደኛ-ሁለተኛ ደረጃ)። (2015፣ መስከረም) ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ ሐዋሳ። (ያልታተመ)

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ (2014) <u>አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ የ7ኛ ክፍል።</u> ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ ሐዋሳ።

---------- (2014) አማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ የመምህሩ መምሪያ 7ኛ ክፍል፡፡ ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ ሐዋሳ፡፡

----------- (2014) አማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ የመምህሩ መምሪያ 8ኛ ክፍል ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ ሐዋሳ፡፡

----------- (2014) አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል፡፡ ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ ሐዋሳ፡፡

ያለው እንዳወቀ (2009) የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ጌታሁን አማረ (1990) ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

----------- (2007) "የአማርኛ ሰዋሰው ትምህርት ይዘትና አቀራረብ - በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ናሙናነት"፡፡ *Journal of Ethiopian studies*, pp.1-34, vol. 49, 2016.

--------- (2013) የአማርኛ ሰዋስው፡፡ *ለአንደኛ ደረጃ፤* አዲስ አበባ፣ ህትመት ጃጃው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃላ.የተ.የግ.ማ፡፡

ፈለቀች እሸቱ (2014) "በደቡብ ክልል ስራ ላይ ባሉ የ5ኛና 6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፡፡" ጂማ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል ለአማርኛ ማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ በከፊል የማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)፡፡

Batstone, R. (1994) Grammar. Oxford: Oxford University Press.

Brown, D. (1994) Principles of language and teaching practice and theory. Cambridge: Cambridge university press.

Cunningsworth, A. (1984) Evaluating and Selecting EFL. Teaching Materials. Oxford: Heinma.

-----------------.(1995) Choosing your course book. Oxford: Heniman.

Grant, N. (1987) Making the most of Your Textbook. London: Longman.

Harmer, J. (1987) Teaching and Learning Grammar. London፡Longman.

Larsen-Freeman, D. (1991) *Teaching Grammar.* In Celce-Murcia,M. (ed.). *Teaching English as Second or Foreign Language*. Boston: Heinman Publisher. PP. 246-295.

Stern, H. H. (1983) FundamentalConcept of LanguageTaching. Cambridge. CUP.

Taba, H. (1962) Curriculum Development Theory and Practice. New York: Hascourt Brace, Jovanovich.

Tyler, R.W. (1949) Basic Principles of Curriculum and Instruction. Chicago: The University of Chicago Press.

Ur, P. (1996) A Course in Language Teaching: Practice and Theory. Cambridge: Cambridge university press.

Woods, E. (1995) Introducing Grammar. London: Penguin.